# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 051 ጥቅምት 21 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## “ኢትዮጵያ በስንዴ ምርት ከፍተኛ ውጤት አስመዝግባለች”

- አኪንውሚ አዴሲና (ዶ/ር)
የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በስንዴ ምርት ከፍተኛ ውጤት አስመዝግባለች ሲሉ የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት አኪንውሚ አዴሲና (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት የዓለም የምግብ ሽልማት ውይይት ላይ ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያን በስንዴ ምርት ራሷን የመቻል ስኬታማ ጉዞ አድንቀዋል፡፡

የስንዴ ምርት እ.አ.አ በ2022/23 የምርት ዘመን ወደ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ማሳደግ የተቻለ ሲሆን በሄክታር ሁለት ቶን ይገኝ የነበረው የስንዴ ምርትም

“ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## የፎቶ ዓውደ ርዕዩ ቀደምቷንና የአሁኗን አዲስ አበባ የሚያሳይ ዶክመንተሪ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በቱሪዝም ሳምንቱ የቀረበው የፎቶ ዓውደ ርዕይ ቀደምቷንና የአሁኗን አዲስ አበባ የሚያሳይ ዶክመንተሪ መሆኑን ጄንጊዝ ፓላት ገለጹ።

በዓለም ለ44ተኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ለ36ተኛ ጊዜ በመስቀል አደባባይ የቱሪዝም ሳምንት ትናንት ተከብሯል። በቱሪዝም ሳምንቱም የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመተባበር የፎቶ ዓውደ ርዕይ በመስቀል አደባባይ ለዕይታ አቅርቧል።

በቱርክ የልማትና ትብብር ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ፕሮግራም ኮርዲኔተር ጄንጊዝ ፓላት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገረው፤ የፎቶ ዓውደ ርዕዩ አዲስ አበባ ትናንትናና ዛሬ ያላትን ለውጥ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ለውጡ ትክክለኛ መንገድን የተከተለ መሆኑን ከፎቶ ዓውደ ርዕዩ ተረድቻለሁ።

የአዲስ አበባን የትናንትና የዛሬ ገጽታ፣ የከተማዋን

የፎቶ ዓውደ ርዕዩ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፎቶ፡ በረሁን ታደሰ





ፎቶ፡ በረሁን ታደሰ

አቶ ጃንጥራር ዓባይ

## ቱሪዝምን ለማሳደግ ያሉትን ፀጋዎች በአግባቡ ማወቅና ማሳወቅ ይገባል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የቱሪዝሙን ዘርፍ እንደ ሀገር ሆነ እንደ ከተማ ለማሳደግና ተጠቃሚነትን ለማስፋት ያሉንን ፀጋዎች በአግባቡ ማወቅና ማሳወቅ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ጃንጥራር ዓባይ ገለጹ።

ለሦስት ተከታታይ ቀናት የሚቆየው የቱሪዝም ሳምንት "ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት፤ አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም!" በሚል መሪ ቃል በትናንትናው ዕለት በመስቀል አደባባይ መከበር ተጀምሯል።

መርሐ ግብሩ ላይ አቶ ጃንጥራር ዓባይ እንደገለጹት፤ የበዓሉ ዓላማ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ኢንቨስት የምናደርግበት ጊዜ አሁን በመሆኑን ማሳያ ነው። ለዚህም ዘርፉን ለማሳደግና ለማዘመን ያሉንን ሀብቶቻችንን ማወቅና ለሌሎች ማሳወቅ ይጠበቅብናል።

አዲስ አበባ ከተማን የቱሪዝም መዳረሻ በማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭ ከተማ እንድትሆን መሥራት ይገባል።

ቱሪዝምን ለማሳደግ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል












## ከ41 ሚሊዮን ቆዳና ሌጦ ግማሹ አገልግሎት ላይ አይውልም

- የ10 ዓመት የቆዳ ልማት ስትራቴጂ ይፋ ሆነ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በዓመት ከሚመረተው ከ41 ሚሊዮን የቆዳና ሌጦ ምርት ግማሽ ያህሉ አገልግሎት ላይ እንደማይውል የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ። የቆዳ ዘርፉን ማነቆዎች ለመፍታት ከ2016 እስከ 2025 ዓ.ም የሚተገበር የ10 ዓመት የቆዳ ልማት ስትራቴጂ ይፋ ተደርጓል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በቆዳ ልማት ስትራቴጂ ሰነድ ላይ ከዘርፉ ባለድርሻ አካላትና አምራች ኢንዱስትሪ ባለቤቶች ጋር ትናንትና ውይይት ሲያካሂድ፤ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር

ከ 41 ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል







# “አሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ገንዘባችንን ወስደው እየጠፉ ነው”

*- ሥራ ፈላጊዎች*

# “ድርጊቱን በሚፈጽሙ ኤጀንሲዎች ላይ ርምጃ ይወሰዳል”

- የአዲስ አበባ የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- አሠሪ ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የምዝገባ ገንዘብ ከወሰዱ በኋላ ቦታ እንደሚቀይሩ እና በሥራ ፈላጊው ላይ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቦናዊ ጉዳት እያደረሱ እንደሆነ ሥራ ፈላጊ ወጣቶች ገለጹ። የአዲስ አበባ የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በበኩሉ፤ የሥራ ፈላጊዎችን ገንዘብ እየወሰዱ የሚጠፉ ኤጀንሲዎችን እንደማይታገስና ተገቢውን ርምጃ እንደሚወስድ ገልጿል።

ሥራ ፈላጊ ወጣት በለጠ አሻግሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገረው፤ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ኤጀንሲዎች ለቅጥር ምዝገባ ከ400 እስከ 600 ብር ገንዘብ ይጠይቃሉ። ነገር ግን በክፍያውና በቅጹ መሠረት ሥራ ከማስቀጠር ይልቅ ተጨማሪ ገንዘብ አምጡ ይላሉ። ከዚህም ባለፈ ሥራ ፈላጊ ወጣቶችን ያንገላታሉ።

አሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎቹ የምዝገባ ገንዘብ ከወሰዱ በኋላ ቦታ እንደሚቀይሩ የገለጸው ወጣት በለጠ፤ ለተማረው የሰው ኃይል ራስ ምታት ሆነዋል፤ በተለይ በተመራቂ ሥራ ፈላጊዎች ላይ የሚያሳድሩት የገንዘብና የሥነ ልቦና ጉዳት ከፍተኛ ነው። ይህም በሰው ሕይወትና ኑሮ ላይ መቀለድ ነው ሲል ገልጿል።

እንደ ወጣቱ ገለፃ፤ የሥራ ማስታወቂያ በሚለጠፍበት ቦርድ ላይ በርካታ የሥራ ማስታወቂያዎች ይለጠፋሉ። ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ የሥራ ቅጥር ማስታወቂያ የሚለጥፉት አሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ናቸው። ኤጀንሲዎቹ በብዛት ሕጋዊ ማኅተም የላቸውም። ነገር ግን የሥራ ማስታወቂያ ቦርዱ ላይ ይለጥፋሉ።

ኤጀንሲዎቹ የተቋቋሙበት ዓላማ ሌብነት በመሆኑ በማስታወቂያው ላይ የሚለጥፉት የደመወዝ መጠን ከፍተኛ ነው። ከዚህም ባለፈ የትራንስፖርትና የቤት ተጨማሪ ክፍያ እንዳለው በማስታወቂያው ይገለፃል ያለው ወጣት በለጠ፤ የኤጀንሲዎቹ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሆኑ የሚመለከተው አካል ርምጃ መውሰድ አለበት ብሏል።

ወጣት ታምራት ተረፈ በበኩሉ፤ የሥራ ፈላጊ ዜጋን ገንዘብ ወስዶ መጥፋት ኢኮኖሚያዊ ጫናው ከፍተኛ ነው። ሥራ ፈላጊው ሥራ ለማግኘት ያለውን ገንዘብ እያባከነ በመሆኑ በኑሮው ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያሳደረበት ነው። በሥነ ልቦናም ደረጃ ተስፋ ያስቆርጣል፡፡ ከዚህ አኳያ ኤጀንሲዎቹ በሀገርና በትውልድ ላይ የሚያሳድሩትን ጉዳት ማስቆም እንደሚገባ አሳስቧል።

ሥራ ፈላጊዎች ለኤጀንሲዎች ገንዘብ መክፈል ያለባቸው ሥራውን ከተቀጠሩ በኋላ መሆን እንዳለበት የገለጸው ወጣት ታምራት፤ ከሥራ ፈላጊ ሰዎች ላይ ገንዘብ ያለአግባብ የሚወስዱ ኤጀንሲዎች በወጣቱ ላይ የሚያሳድሩት ጉዳት መጠነ ሰፊ በመሆኑ ይህንን እኩይ ተግባር ሁሉም በጋራ ሊከላከለው እንደሚገባ አስገንዝቧል።

መንግሥት ሕገወጥ ኤጀንሲዎችን ተከታትሎ ሕጋዊና ተመጣጣኝ ርምጃ ሊወስድ ይገባል ያለው ደግሞ ወጣት ካሣዬ ጋሻው ነው።

ኤጀንሲዎቹ የሚሠሩት ሥራ ሰብዓዊነት የጎደለው ተግባር በመሆኑ ሥራ ፈላጊውን ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እየከተቱት ነው ያለው ወጣት ካሣዬ፤ የኤጀንሲዎቹ ቁጥር በከተማዋ እየጨመረ በመምጣቱ ከወዲሁ ርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚገባ ገልጿል።

የአዲስ አበባ የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በበኩሉ፤ የሥራ ፈላጊዎችን ገንዘብ እየወሰዱ የሚጠፉ ኤጀንሲዎችን እንደማይታገስና ተገቢውን ርምጃ እንደሚወስድ ገልጿል።

በቢሮው የሥራ ስምሪት ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ ሰብሀዲን ሡልጣን እንደተናገሩት፤ ቢሮው በኤጀንሲዎች የቁጥጥርና የክትትል ሥራ እየሠራ ነው። አምና በ109 አሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ላይ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ደግሞ በሁለት ኤጀንሲዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል።

ኅብረተሰቡ ሕገወጥ ኤጀንሲዎችን ሲያገኝ ለቢሮው እንዲጠቁም ጠይቀው፤ በሕገወጥ ኤጀንሲዎች ላይ የሚወሰደው ርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል። ይህም ተግባር ዝም ተብሎ የማይታለፍ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ኅብረተሰቡ ከሥራ ፈላጊዎች ገንዘብ ወስደው የማይቀጥሩ ኤጀንሲዎችን በአቅራቢያው በሚገኝ የወረዳ ደንብ ማስከበር ጽሕፈት ቤት ሊያሳውቅ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ጽሕፈት ቤቱም እጅ ከፍንጅ እንዲያዙ እንደሚያደርግ ገልጸው፤ ቢሮው ደግሞ የተያዙትን ኤጀንሲዎች መርምሮ ርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል ብለዋል።

በሥራ ፈላጊዎች ላይ የሚደርስ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቦናዊ ጉዳት ሀገርንና ትውልድን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ በቀላሉ የሚታለፍ ጉዳይ አለመሆኑን ገልጸዋል።

# በቀጣይ ዓመት ነባር ክልሎች ወደ ኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት ይገባሉ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ ዓመት አዳዲስ ከተቋቋሙ ክልሎች በስተቀር ነባር ክልሎች ወደ ኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት እንደሚገቡ የግዢና ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ።


የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት በ165 ፌዴራል ተቋማት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል።

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሐጂ ኢብሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2017 ዓ.ም በኢትዮጵያ ከተቋቋሙ አዲስ ክልሎች በስተቀር ሁሉንም ነባር ክልሎች ወደ ኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት እንዲገቡ ይደረጋል።

እንደ ሐጂ ኢብሳ ገለጻ፤ በዘንድሮው ዓመት የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓቱን በሲዳማ ክልል ዘጠኝ ተቋማት ላይና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጀምሯል።

ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሐረሪ፣ አፋር፣ ሶማሌ፣ ጋምቤላና ሌሎችም ነባር ክልሎች ወደኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት እንዲገቡ ይደረጋል።

ባለፈው ዓመት 70 የመንግሥት ተቋማት በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት ግዢ መፈጸማቸውን የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዘንድሮ ዓመት 165ት ተቋማት የግዢ ሥርዓቱን መቀላቀላቸውን አመላክተዋል።



**ሐጂ ኢብሳ**

በ2015 ዓ.ም 100 አቅራቢዎች በግዢ ሥርዓቱ ተመዝግበው እንደነበር አስታውሰው፤ በአሁኑ ሰዓት 15 ሺህ በላይ አቅራቢዎች መመዝገባቸውን ተናግረዋል፡፡

በዘንድሮው ሩብ ዓመቱ ከ30 ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት በኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት እንደሚፈጸም ገልጸዋል።

የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓቱ በፌዴራል ተቋማት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆኑን የገለጹት ሐጂ ኢብሳ፤ ለአራት የትግራይ ዩኒቨርሲቲዎችን ተገቢውን ሥልጠና በመስጠት ወደ ሥርዓቱ ለማስገባት እየተሠራ ነው ብለዋል።

የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት ብልሹ አሠራርን፣ ሌብነትንና አድሎና ለማስቀረት እንደሚያስችል ጠቁመው፤ በተለይም በማንዋል በሚሠራበት ወቅት ለወረቀትና ለተለያዩ ግብዓቶች ይውል የነበረውን ወጪ ለማስቀረት ይረዳል ሲሉ አስረድተዋል።

ኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓቱ ፍትሐዊ የንግድ ሥርዓትን ለማስፈን የሚረዳ መሆኑን ተናግረው፤ ቀደም ሲል የተወሰነ ሰው አገልግሎቱን ለመስጠት የሚመዘገቡበትን ኋላቀር አሠራር በማስቀረት ለየትኛውም ሰው በተመሳሳይ ሰዓት እኩል የሚደርስ የዲጂታል አማራጭ መሆኑን ሐጂ ኢብሳ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም የፌዴራል ተቋማት የትኛውንም ግብይት በማኑዋል ሥርዓት መግዛት እንደማይችሉ የገለጹት፤ ዋና ዳይሬክተሩ፤ በኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓቱ መሳተፍ የሚፈልግ የንግዱ ማኅበረሰብም የግብይት ሥርዓቱን በተመለከተ ለሥልጠና የተዘጋጀ ቦታ በመኖሩ በጉዳዩ ላይ በቂ ግንዛቤ ማግኘት የሚችል መሆኑን አመላክተዋል።



**ወይዘሮ ዛሕራ ሁመድ**

# በዓሉ ኅብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓቱ ለሰላም ግንባታ ያለውን ሚና በሚያጠናክር መልኩ ይከበራል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የዘንድሮው የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል ኅብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓቱ ለዘላቂ ሰላም ግንባታ ያለውን ሚና በሚያጠናክር መልኩ እንደሚከበር የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይዘሮ ዛሕራ ሁመድ ገለፁ።

በሶማሌ ክልል አዘጋጅነት በጅግጅጋ ከተማ ለሚከበረው 18ኛው የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል በፌዴሬሽን ምክር ቤት አስተባባሪነት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጀምረዋል።

በዓሉን ሕገ መንግሥቱንና ኅብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓቱ አስተምህሮን በአግባቡ ተደራሽ ባደረገ መልኩ ለማክበር የአሠልጣኞች ሥልጠና ዛሬ በአዳማ ከተማ ተሰጥቷል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ ወይዘሮ ዛሕራ ሁመድ በመድረኩ መክፈቻ ላይ እንደገለጹት፤ በዓሉ ቀኑን ከማሰብ ባለፈ ሕገ መንግሥታዊ ቃል ኪዳን የሚታደስበት ነው።

ቀኑን ከማሰብ ባለፈ ኅብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓቱ ለዘላቂ ሰላም ግንባታ ወሳኝ ሚና እንዳለው በማረጋገጥ ጭምር እንደሚሆን ተናግረዋል።

ኅብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓቱ ለሕዝቦች እኩልነት፣ ነፃነትና አንድነት ዋስትና የሰጠ መሆኑን ያስታወሱት ወይዘሮ ዛሕራ፤ በዓሉ ብዝኃነትን፣ መቻቻልንና አብሮነትን በማጎልበት ዴሞክራሲና ዘላቂ ሰላምን የምናጠናክርበት ነው ብለዋል።

ለዘመናት አስተሳስረውን የኖሩት እሴቶቻችን የሀገራችንን አንድነት ማፅናት ችለዋል ያሉት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ፣ በዓሉ የብሔር ብሔረሰቦችን ባሕልና እሴቶች ለማጎልበት ፋይዳ እንዳለውም አመልክተዋል።

ሥልጠናው በዓሉን ምክንያት በማድረግ በቀጣይ በፌዴራሊዝም እና ሕገ-መንግሥታዊ አስተምህሮ ላይ አካታች መድረኮችና ውይይቶች ለማዘጋጀት ያለመ መሆኑን ጠቁመዋል።

በፌዴሬሽን ምክር ቤት የመንግሥታት ግንኙነት፣ የዴሞክራሲ አንድነትና የሕገ መንግስት አስተምህሮ ቋሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ወይዘሮ ባንችይርጋ መለሰ በበኩላቸው ኅብረ-ብሔራዊ አንድነትና ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በትኩረት እየተሠራ ነው።

በብዝኃነት መካከል እኩልነት፣ አንድነት፣ ዴሞክራሲና ሰላምን ለማፅናት ኅብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓቱ ወሳኝ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ጠቁመዋል።

"በዓሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ትስስራቸውን የሚያጠናክሩበት በመሆኑ ሀገራዊ አንድነትን ይበልጥ ለማጎልበት ሚናው የጎላ ነው" ብለዋል።

በመድረኩ ላይ ከሁሉም ክልል እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች የመጡ ምክትል አፈ-ጉባኤዎች ተሳታፊ መሆናቸውን ገልጸዋል። በዓሉ በየዓመቱ የሚከበረው የሕዝቦችን ሕገ መንግሥታዊ ቃል ኪዳን ለማደስ ጭምር መሆኑን ተናግረዋል።

ለፌዴራል ሥርዓቱ አዎንታዊ አበርክቶ ባላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አደረጃጀቶች የሚሳተፉባቸው መድረኮች እንደሚካሄዱም ጠቅሰዋል።

በበዓሉ የፌዴራል ሥርዓቱ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ እና ብዝኃነት እንደፀጋ በመቀበል የሚኖረውን ፋይዳ ለማስገንዘብ እንደሚሠራም ገልጸዋል።

በተጨማሪም በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠው የሕዝቦች ነፃነትና እኩልነት ማክበር ለሀገራዊ አንድነትና ዘላቂ ሰላም መሠረት መሆኑን አፅንዖት የሚሰጥበት እንደሆነ ተናግረዋል።

18ኛው የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በሀገር አቀፍ ደረጃ በመጪው ኅዳር 29 ቀን 2016 ዓ.ም በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ እንደሚከበር ታውቋል።



## እንደ ክልል ያጋጠመውን የሰላም እጦት በዘላቂነት ለመፍታት የክልሉ መንግሥት በትኩረት እየሠራ ነው

- ርዕሰ መስተዳድር አረጋ ከበደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ ፤ እንደ ክልል ያጋጠመውን የሰላም እጦት በዘላቂነት ለመፍታት የክልሉ መንግሥት በትኩረት እየሠራ ነው ሲሉ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አረጋ ከበደ ገለጹ፡፡

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አረጋ ከበደ በሀገራዊና ክልላዊ ሁኔታዎች ዙሪያ ከተለያዩ አካላት ጋር ትናንት በደሴ ከተማ ውይይት አድርገዋል፡፡

በውይይቱም የወሎና አካባቢው ማኅበረሰብ ከፀጥታ አካላት ጋር በመኾን የአካባቢውን ሰላም የሚጠብቅበት መንገድ ለሌሎች አካባቢዎችም ተሞክሮ እንደሚኾን ነው የገለጹት፡፡

የደሴና አካባቢው ማኅበረሰብ እንደሌሎች አካባቢዎች ሁሉ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች እንዳሉት ርዕሰ መስተዳደር አረጋ ከበደ ተናግረዋል፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ ኅብረተሰቡ ጥያቄዎቹን በየደረጃው በሰላማዊ መንገድ በማቅረብ እና የአካባቢውን ሰላም በማስጠበቅ እያደረገ ስላለው አስተዋፅዖ በክልሉ መንግሥት ስም አመስግነዋል፡፡

እንደ ክልል ያጋጠመውን የሰላም እጦት በዘላቂነት ለመፍታት የክልሉ መንግሥት በትኩረት እየሠራ መኾኑን ማንሳታቸውን የአሚኮ ዘገባ ያመላክታል፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ መንግሥት ከሕዝቡ ጋር በመተባበር እየወሰደው ባለው እርምጃና በተደረገው ውይይት ክልሉን ወደ ሰላም ለማምጣት እየተሠራ መሆኑንም አስገንዝበዋል፡፡

የውይይቱ ተሳታፊዎችም ርዕሰ መስተዳድሩ በወቅታዊ ጉዳይ ላይ በደሴ ከተማ ተገኝተው ከኅብረተሰቡ ጋር መወያየታቸው እንዳስደሰታቸው ተናግረዋል፡፡

ከግጭት አዙሪት በመውጣት ሁሉም ለሰላም ቅድሚያ ሊሰጥ እንደሚገባ ጠቁመው አንድነትን በማስቀጠል ኅብረ ብሔራዊነትን ማስጠበቅ አለብን ሲሉም ገልጸዋል፡፡

የአማራ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አብዱ ሁሴን በበኩላቸው፤ "የክልሉን የስንዴ ምርታማነት ለመጨመር አርሶ አደሮች ግብዓት በወቅቱ እንዲደርሳቸውና ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች እንዲኖራቸው እንሠራለን ብለዋል።

የስንዴ ልማት ሀገራችን በምግብ ራሷን እንድትችልና ከልመና እንድትላቀቅ የሚያስችል ተኪ የሌለው ሥራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የክልሉ መንግሥትም የስንዴ ምርታማነትን ለመጨመር አርሶ አደሮች ግብዓት በወቅቱ እንዲደርሳቸውና ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች እንዲኖራቸው ይሠራል ሲሉ አመላክተዋል።

ምክትል ርዕሰ መስተዳደሩ እንደገለጹት፤ የግብርና ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ የማስጠበቅ ሥራ በትኩረት ይሠራል።

በምክትል ርዕሰ መስተዳደር ማዕረግ የአማራ ክልል የገጠር ልማት ዘርፍ አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ ድረስ ሣህሉ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የክልሉን ሕዝብ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ትኩረት ተሠጥቶት እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በምርት ዘመኑ በክልሉ ከ250 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ በዘር ይሸፈናል። ከዚህም ከዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል ሲሉ ዶክተር ድረስ ተናግረዋል።

በስንዴ ዘር ማስጀመሪያ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የአማራ ክልል ምክትል ርእሰ መስተዳደር አብዱ ሁሴን፣ በምክትል ርዕሰ መስተዳደር ማዕረግ የአማራ ክልል የገጠር ልማት ዘርፍ አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ ድረስ ሣህሉ (ዶ/ር) ጨምሮ የዞን እና የወረዳ የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል፡፡

## በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ 53 ሄክታር መሬት ለመንግሥት ተመላሽ እንዲሆን ተደርጓል

### - በ26 አመራሮች ላይ ርምጃ ተወስዷል

**ሞገስ ተስፋ እና ሙሉቀን ታደገ**

አዲስ አበባ፡- በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የመሬት ወረራን ለመከላከል በተወሰደው እርምጃ በ2015 በጀት ዓመት 53 ሄክታር ወደ መሬት ባንክ ገቢ መደረጉን የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታረቀኝ ገመቹ ገለጹ፡፡

በክፍለ ከተማው ብልሹ አሠራር ውስጥ የተገኙ 26 አመራሮች ላይ አስተዳደራዊ ርምጃ የተወሰደ ሲሆን፤ ከሕገ ወጥ ድርጊቶች ቅጣትም አንድ ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ መደረጉንም ጠቁመዋል፡፡

አቶ ታረቀኝ እንዳስታወቁት፣ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በመሬት ላይ ያለውን ሕገ ወጥነት ለመከላከል አመራሩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ ነው፡፡ በዚህም ከመሬት ወረራ ጋር በተገናኘ አንድ ሺህ 299 ሕገ ወጦች ተለይተው በተወሰደ ርምጃ 53 ሄክታር ወደ መሬት ባንክ ገቢ ተደርጓል፡፡

ከመሬት ማስፋፋት አኳያ ደግሞ ካላቸው መሬት ጨምረው መሬታቸውን አስፍተው የያዙ 52 ሰዎች ተለይተው አራት ሺህ 973 ካሬ ሜትር ተመላሽ ተደርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ታረቀኝ ገለጻ፤ በክፍለ ከተማው የሚታዩ



ችግሮችን ከመፍታት አኳያ ሰባት የሚሆኑ ግብረ ኃይሎች የተቋቁሙ ሲሆን፤ የኑሮ ውድነትን ከሚያባብሱና ከፕሮጀክቶችንም ጋር የተያያዙ ብልሹ አሠራርና ሌብነት፣ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ችግሮች የሚከታተሉ ኮሚቴዎች ተደራጅተው ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

በመቶ ቀን ዕቅድ ውስጥ ሕገ ወጥነትንና የመሬት ወረራን ከመከላከል አንጻር በፀጥታ አስተዳደር የሚመራ ቡድን የተቋቋመ መሆኑን የገለጹት አቶ ታረቀኝ፤ ሥራውም በየሳምንቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚው በተገኙበት የሚገመገም መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በዚህም በሕገ ወጥ የጎዳና ላይ ንግድ፣ በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት እና በሕገ ወጥ እንስሳት እርድ በኩልም እርምጃ መወሰዱን፤ ከዚህም አንድ ሚሊዮን 193ሺህ 325 ብር በቅጣት ገቢ መደረጉን አመላክተዋል።

በሌላ በኩል በክፍለ ከተማው ያሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ላይ በተደረገ ልየታ በአመራሮች ላይ እርምጃ መወሰዱን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ በዚህም ቦታ ከመቀየር ባለፈ ችግር ያለባቸው ከአመራርነት እንዲነሱ መደረጉን አስረድተዋል፡፡

በወረዳ 13 እና ወረዳ 06 ላይ አዲት ተደርጎ በብልሹ አሠራር ውስጥ የተገኙ አመራሮች በግምገማ መነሳታቸውን በማሳያነት በመጥቀስም፤ ከአመራሩ በተነሳ ሀሳብም ሆነ ከኅብረተሰቡ በተገኘው ጥቆማ መሠረት 26 ሰዎች ከአመራርነት እንዲነሱ መደረጉን ተናግረዋል፡፡

አሁንም የቀሩ አመራሮች ሁሉም ንጹሕ ናቸው ማለት አይቻልም ያሉት አቶ ታረቀኝ፤ በቀጣይም በዚህ ላይ ብዙ ሥራ የሚጠይቅ እንደመሆኑ እርምጃው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

በዚህና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከአቶ ታረቀኝ ጋር ያደረግነው ሙሉ ቃለ ምልልስ በተጠየቅ ዓምዳችን ላይ ያገኙታል፡፡



## በኦሮሚያ 2 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄክታር አሲዳማ መሬት ሕክምና ያስፈልገዋል

**ማርቆስ በላይ**

ጉደር፡- በኦሮሚያ ክልል ለእርሻ ከሚውለው መሬት ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታሩ በአሲዳማነት በመጠቃቱ የአፈር ሕክምና እንደሚያስፈልገው የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ አሲዳማ የእርሻ መሬትን በማከም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሁሉን አቀፍ ሥራ እየተሠራ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን የጉደር ኖራ ማምረቻ ፋብሪካና በክልሉ አሲዳማ መሬትን በኖራ ለማከም እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ትናንትና ተጎብኝተዋል።

የኦሮሚያ ክልል ምክትል የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኤሊያስ ከድር እንደገለጹት፤ በኦሮሚያ ክልል ለእርሻ ከሚለው መሬት ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬቱ አሲዳማ ነው።

በክልሉ አሲዳማ የእርሻ መሬትን በማከም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሁሉን አቀፍ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ኤሊያስ፤ በተለይም ቴክኖሎጂን ለአርሶ አደሩ በማስተማር ኖራን እንዲጠቀሙ እየተደረገ ነው ብለዋል።

ባለፉት ጊዜያት አሲዳማ መሬት ያለባቸው አካባቢዎች የመለየት ሥራ መሠራቱን ጠቅሰው፤ በልየታው መሠረት በክልሉ በ15 ዞኖች 154 ወረዳዎች በአፈር አሲዳማነት እንደተጠቁ መታወቁን አመልክተዋል።

የመሬት አሲዳማነትን ለማከም የኖራ ፋብሪካ ተቋቁሞ በሥራ ላይ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ በ257 ሚሊዮን ብር ተጨማሪ ማሽኖች ተገዝተው ኖራ በማምረት ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የኖራን ምርትና የአርሶ አደሩን ፍላጎት ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን የገለጹት አቶ ኤሊያስ፤ በኖራ ፋብሪካው በዘንድሮው ዓመት 150 ሺህ ኩንታል ለማምረት እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በክልሉ ኖራን በመጠቀም የመሬት አሲዳማነትን ለመቀነስ እንደሚያስችል የተቀናጀ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አመላክተው፤ የአፈር ሕክምናው ምርትና ምርታማነትን በመጨመር የአርሶ አደሩን ከገጠር ወደ ከተማ ስደት ለመቀነስና እንደሚያስችል ገልጸዋል።

የጉደር ኖራ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ ፊጣ ኩምሳ በበኩላቸው፤ በኖራ ፋብሪካው አምስት ማሽኖች በሥራ ላይ መሆናቸውን ተናግረው፤ በቀን አንድ ሺህ 600 ኩንታል ኖራ እየተመረተ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በዘንድሮው ዓመት ከመስከረም ጀምሮ 40 ሺህ ኩንታል ኖራ ማምረት ተችሏል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ በዓመቱ መጨረሻ ለአሲዳማ አፈር ሕክምና የሚውል 300 ሺህ ኩንታል ለማምረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ፋብሪካው ለአካባቢው ማኅበረሰብ የሥራ ዕድል መፍጠሩን ገልጸው፤ ከ172 በላይ ሰዎች በቋሚና በጊዜያዊነት የሥራ ዕድል ማግኘታቸውን አስታውቀዋል።

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን በተደረገው ጉብኝት ላይ የክልሉ ከፍተኛ አመራሮችን ጨምሮ የዞንና የወረዳ ግብርና ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የፓርቲዎቹ ውሳኔ ለሀገራቸው ብሩህ ነገዎች ያላቸውን ቀናኢነት ያመላከተ ነው!

ለአንድ ሀገር ዘላቂ ሰላም እና መረጋጋት፤ ልማት እና ብልጽግና የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁለንተናዊ አበርክቶ ከፍ ያለ ነው። ከሁሉም በላይ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ በመገንባት ሂደት ውስጥ የሚኖራቸው የጋራ ኃላፊነት መተኪያ የሌለው ነው፤ የስኬታማነታቸው ዋነኛ መመዘኛም ይህንኑ ኃላፊነታቸው በአግባቡ የመወጣታቸው እውነታ እንደሆነም ይታመናል።

በተለይም ለረጅም ዘመናት አምባገነናዊ በሆኑ የፖለቲካ አስተዳደሮች ውስጥ ያለፉ፤ በዚህም ብዙ ዋጋ ለመክፈል የተገደዱ ሕዝቦች፤ ወደ ዴሞክራሲ ሥርዓት የሚያደርጓቸው የሽግግር ጉዞዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች አንድ ሀገራዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ግንባር ቀደም መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ለዚህም ልዩነትን የሚያሰፉ፤ ቁርሾና ግጭት ቀስቃሽ ከሆኑ ትርክቶች ወጥተው፤ እንደ ሀገር ሕዝብን አንድ የሚያደርጉ፤ ሕዝቡ የለውጥ አስተሳሰቦችን ተቀብሎ ዋነኛ የለውጥ ኃይል የሚሆኑበትን የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር፤ ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት፣ አስተሳሰባዊ ልዕልና እና ቁርጠኝነት መፍጠር ይኖርባቸዋል።

ትናንቶችን ከውዥንብሮች ማጥራት፤ ከጠሩ ትናንቶች መማር፤ ዛሬን የተሻለ፤ ነገን ደግሞ ባለ ብዙ ተስፋ ማድረግ የሚያስችል አዲስ ለውጥ ተሸካሚ ትርክት መፍጠር፤ በዚህ ትርክት የተፈጠረና የተገዛ አንድ ሀገራዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል ።

ይህም እንደ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ እንወክለዋለን የሚሉትን ሕዝብም ሆነ የማኅበረሰብ ክፍል ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ ባለፈ፤ እንደ ሀገር ለሁሉም ዜጎች ለኑሮ የተመቸች ሀገር ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ትልቅ አቅም የሚፈጥርላቸው ነው ።

በተለይ እንደኛ ባሉ፤ ብሔራዊ አንድነትን የሚሸረሽሩ የተዛቡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ትርክቶች በበዙባቸው፤ በተዛቡ ትርክቶች ምክንያት ሰላምና መረጋጋት እያጡ ባሉ ሀገራት፤ አንድ ሀገራዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሚደረጉ ጥረቶች በብዙ ፈተናዎች የተሞሉ ስለመሆናቸው ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት ከሁሉም በፊት እነዚህን ትርክቶች ማጥራት ወሳኝ ነው፤ ትርክቶችን በማጥራት ሂደትም እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ፤ ትናንቶችን በሁለንተናዊ መልካቸው ተገንዝቦ፤ ለዛሬ ሀገራዊ የልማትና የብልጽግና ጉዞ አቅም ፤ ለነገ ደግሞ የተጨባጭ የተስፋ ምንጭ የሚሆኑበትን ዕድል መፍጠር ይኖርባቸዋል ።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ትናንቶችን የማጥራትና የማከም ሁኔታ ከአሁናዊ የሥልጣን ጥያቄ ያለፈ ሀገርን የማቆምና የማጽናት አጀንዳ መሆኑን መረዳት፤ ይህንኑ አጀንዳ ከየትኛውም ሀገራዊ አጀንዳ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ እና ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ ሊከናወን እንደሚገባ ሊያጤኑት ይገባል።

የለውጡ መንግሥት ወደ ሥልጣን በመጣ ማግስት ለዚህ ሀገራዊ አጀንዳ ቅድሚያ በመስጠት የቀደሙ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ትርክቶቻችንን ማጥራትና ማከም እንችል ዘንድ ነፃ የሆነ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አዋቅሯል ። ኮሚሽኑም ወደ ሥራ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ በመንቀሳቀስ ተስፋ ሰጭ መንገድ ላይ ይገኛል።

እንደሚታወቀው፤ ኮሚሽኑ ሲቋቋም አብረውት ለመሥራት ፈቃደኛነታቸውን ያሳወቁት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር ሦስት ነበር፤ ይህ አኃዝ ደግሞ ብዙዎችን ያሳሰበ እንደነበር የሚታወስ ነው ።

የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ለኮሚሽኑ ተልዕኮ ስኬት ከነበራቸው አዎንታዊ አስተዋፅዖ አንጻር በርግጥም መረጃው አስደንጋጭ ነበር ፤ ይሁንና ኮሚሽኑ ደረጃ በደረጃ ባከናወናቸው ሥራዎችና በፈጠረው ቅርርብ በአሁኑ ጊዜ በምርጫ ቦርድ ከተመዘገቡ 53 የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ 47ቱ ከኮሚሽኑ ጋር አብሮ ለመሥራት የስምምነት ማዕቀፍ ተፈራርመው እየሠሩ ነው፡፡

በተለይም የፖለቲካ ፓርቲዎች ትናንቶችን በማጥራት፤ ከትናንት ተገቢውን ትምህርት ወስዶ ዛሬ ላይ አዲስና ዘመኑን የሚዋጅ የፖለቲካ ሥርዓት እና እሱን የሚሸከም ትርክት በውይይት/በንግግር ለመፍጠር የደረሱበት ድምዳሜ ከፍ ያለ ዕውቅናና ከበሬታ የሚሰጠው ነው። እንወክለዋለን ለሚሉት ሕዝብና የማኅበረሰብ ክፍል ከዚያም በላይ ለጋራ ለሆነችው ሀገራቸው ብሩህ ነገዎች ያላቸውን ቀናኢነት ያመላከተ ጭምር ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የቡና ሰንሰለት ተዋናዮችን ወደፊት ለማራመድ!

ሰላማዊት ውቤ

ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ሀገር ነች። ለፈጣሪ ምስጋና ይግባውና ለቡና ተስማሚ የሆነ ሰፊና ለም መሬት እንዲሁም የአየር ንብረት ችሯታል። ወደ 90 በመቶ የሚጠጋው የኮፊ ዐረቢካ ዝርያ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን እየተካሄዱ ያሉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ገና ተጨማሪ ዝርያዎች እንደሚኖሩ ይጠበቃል። ምርቱ የሀገር ኢኮኖሚ ዋልታ ከመሆን ባለፈ በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ዜጎች ኑሮም ወሳኝ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

አሁን ላይ የቡና የምርት ሰንሰት ውስጥ፤ በመበጠስ፤ በመልቀም፤ በማጓጓዝ በመገበያየት፤ በማቀነባበር እንዲሁም በጥሬውም ሆነ እሴት በመጨመር ወደ ውጭ በመላክ 20 ሚሊዮን የሚያህሉ ዜጎች ኑሯቸውን መሰርተዋል። ከእነዚህ ዜጎች መካከል አብላጫውን ቁጥር የያዙት ሴቶች ናቸው። ሙያውን በቀለሙ ትምህርትም ሆነ በልምድ ደህና አድርገው እንዳካበቱትም በተጨባጭ በመስክ የሚታይ እውነታ ነው።

ተሳትፏቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ አሁን ላይ ከ75 በመቶ በላዩን የሚሆነውን እንደያዙት መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ሆኖ ግን አሁን ድረስ እንደተሳትፏቸው በዘርፉ እየተጠቀሙ አይደለም። በተለይም ከፍ ባለ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶች ቁጥር በእጅጉ ዝቅተኛ ነው።

ከቡናና ሻይ ባለሥልጣን የወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ቡናን ወደ ውጭ በመላኩ በኩል የሚሳተፉት ሴቶች ቁጥር ከ10 በመቶ አይበልጥም። አብዛኞቹ ሴቶች ታች ካለው ከለቀማ ጀምሮ በትንንሽ የቡና እሴት ሰንሰለት ሥራዎች የሚሳተፉ ናቸው።

ለዚህ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሯቸውም ዋናው ተግዳሮት የካበተ የፋይናንስ አቅም አለመኖር ነው። ይህንን አቅም ለማካበት የቱንም ያህል ቢጥሩም በመስኩ ጥቂት ወንዶች የደረሱበት እድገት ማማ ላይ የመድረሱ ጉዳይ ሊሳካላቸው የቻለ አይደለም። ችግሩን ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በቅንጅት መፍታት የሚያስችል ዕድል ቢኖርም በተቋማቱ የሚታየው ቢሮክራሲ ተጨባጭ ሊያደርገው አልቻለም።

በዘርፉ ሰፊ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች እንደሚሉት፤ አንጋፋውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጨምሮ በሀገር ውስጥ አሉ የሚባሉ ባንኮች ገንዘብ የሚያበድሩት ትልልቅ ሕንፃ ላላቸውና በቂ ሀብት ላካበቱ ባለሀብቶች ብቻ ነው።

በቡና ላይ ዕውቀት ኖሯቸው በዚሁ ዕውቀታቸው ለሀገራቸው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ለሚችሉ በዘርፉ ለተሰማሩ ሴት ነጋዴዎች አይደለም። እነዚህ ሴት ነጋዴዎች ለባንኮቹ ጥያቄ የሚሆን ሀብት የሌላቸው በመሆኑ በዘርፉ የማደግ ህልማቸውን እየቀጨጨ ሄዷል።

ዘርፉ ትልቅ የፋይናንስ አቅም የሚጠይቅ መሆኑ፤ ከተከላ እስከ ለቀማ ያለው ሂደት ከሦስት አሥርት ዓመታት በላይ የሚወስድ መሆኑ፤ በዘርፉ ያለውን የሴቶች ኢንቨስትመንት በእጅጉ ፈታኝ አድርጎታል። በዚህም በህልማቸው ልክ በዘርፉ ተሰማርተው የሚጠብቁትን ጥቅም ማግኘት አልቻሉም።

አብዛኞቹ በዘርፉ የተሰማሩ ሴቶች ህልም ቡናን በሰፋፊ እርሻ ላይ የማልማት፤ ለውጭ ገበያ ማቅረብ በዚህም ከፍተኛ የዕድገት ማማ ላይ መውጣትና የሀገራቸውን ስም ማስጠራት ቢሆንም በገንዘብ እጦት ህልማቸው መክኗል።

በአጠቃላይ በቡና ዘርፍ የተሰማሩ ሴቶች እንደ ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ሴት ሥራ ፈጣሪዎች፣ አምራቾች፣ የንግድ ተቋም ባለቤቶችና መሪዎች በተደራረቡ ችግሮች እየተፈተኑ ያሉ ናቸው።

ችግሮቻቸው ከብድር አቅርቦት፣ ከወለድ ምጣኔና ከእፎይታ ጊዜ፣ ዘላቂ የገበያ ትስስር በመሆናቸው ፈተናውን በእጅጉ አበርትተውባቸዋል።

ለሥራቸው የሚያስፈልጓቸውን ሥልጠናዎች በበቂ ሁኔታ ከማግኘት ጋር የተገናኙ ተግዳሮቶቻቸውም ብዙ ናቸው። ሌላው ቀርቶ የመረጃ ተደራሽ አይደሉም። ይህም ባሰቡት ልክና ፍጥነት ተቋሞቻቸውን እንዳያሳድጉና በድካማቸው ልክ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ትልቅ ማነቆ ሆኖባቸዋል።

በቅርቡ በስካይላይት ሆቴል የተከፈተውና በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ በቡና እሴት ሰንሰለት ውስጥ ተዋናይ የሆኑ የሀገራችን ሴቶችን ያሳተፈው የቡና ኮንፈረንስ ይሄንን ችግራቸውን ይፈታል ተብሎ ታምኖበት ሲካሄድ ቆይቷል።

ኢንተርናሽናል ውመን ኢን ኮፊ አሊያንስ ቻፕተር አባል በሆነው ውመን ኢን ኮፊ ኢትዮጵያ ማኅበር ሃሳብ አመንጪነትና አስተባባሪነት የተዘጋጀው ኮንፈረንሱ በፋይናንስ ተግዳሮት ሳቢያ በሥራቸው ለውጥ ባለማምጣት ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ እንቅስቃሴ ያሉ ሴቶችን በመታደግ ረገድ ብዙ ተስፋ የተጣለበት ነው።

በርግጥ ሴቶች በመረጡት መስክ መሥራት የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ከተፈጠረላቸው መብቶቻቸው ከተከበሩላቸው፣ ችግሮቻቸው ከተቀረፉላቸው፣ ጥረታቸውን ካበረታቱላቸው፣ ላበረከቱት አስተዋጽዖ ተገቢው ዕውቅና ከተቸራቸው ፈጣን ለውጥም ያመጣሉ።

ያላቸውን እምቅ አቅምና ተሰጥዖ፤ እውቀትና ክህሎት በሚገባ አውጥተው በመጠቀምም የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ሕይወት ከመለወጥ ባለፈ ለማኅበረሰብ ሁለንተናዊ ለውጥና ለሀገር እድገት ጉልህ አስተዋጽዖ ያበረክታሉ። ይህንን ታሳቢ በማድረግም፤ በመንግሥት በኩል በኢኮኖሚው መስክ ሴቶችን ለማብቃት ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ለሴቶች መብት መከበር ብሎም ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት መረጋገጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያበረከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ተቀብሎ ማጽደቁ ለዚሁ ማሳያ ነው።

በኢፌዴሪ ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩልም የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያግዙ ልዩ ልዩ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፓኬጆችና ሌሎች የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀርፀዋል። ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩም ያላሰለሰ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ከዚህ ባሻገርም መንግሥት የተቀረጹት ሀገራዊ የሕግና የአሠራር ማዕቀፎች ስኬታማ እንዲሆኑ የደጋፊነት ሚናውን እየተወጣ ይገኛል። ሆኖም እንስቶቹ በመስኩ እየገጠሟቸው ያሉ የፋይናንስና ሌሎች ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍ በመንግሥት ብቻ የሚደረግ ጥረት በቂ አይደለም። በዘርፉ የተሰማሩ ተዋናዮችን ጨምሮ የልማት አጋራት፣ የግል ባለሀብቶችና የሌሎችንም የጋራ ትብብርና ርብርብ ይጠይቃል።

ከዓለም የተውጣጡ 33 ሀገራት የተሳተፉበትን ኮንፈረንስ በኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ ማካሄድ ያስፈለገበት ዋና ዓላማም ይሄ እንደሆነ ውመን ኢን ኮፊ ኢትዮጵያ ማኅበር መረጃ ያሳያል። ማኅበሩ የኮንፈረንስ ዝግጅት ሃሳቡን ያመነጨና የተገበረው በብዙ ምክንያት ነው።

አሁን ላይ በመስኩ እየታየ ያለውን መልካም ጅማሮ ዘላቂነት ባለው መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ ፍትሐዊ ተሳትፎና የላቀ ተጠቃሚነት እንዲሰፍን፤ በዚህም የሴቶች የኑሮ ደረጃ እንዲሻሻል ብሎም ሴቶች ለማኅበረሰባቸውና ለሀገራቸው ሁለንተናዊ እድገትና ብልጽግና የሚጠበቅባቸውን ወደር የለሽ ሚናቸውን በሚገባ እንዲጫወቱ ማስቻል ቀዳሚው ትኩረቱ ሊሆን ይገባል።

# ተጠየቅ

# «ሌብነትና ብልሹ አሠራር ውስጥ ገብተዋል ተብለው የተለዩ ከአመራርነት እንዲነሱ ተደርጓል »

**- አቶ ታረቀኝ ገመቹ፣**
**የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ሞገስ ተስፋ እና ሙሉቀን ታደገ

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት፣ "ለሚ ኩራ" በሚል ስያሜ 11ኛ ክፍለ ከተማ ካደራጀ እና መዋቅር ፈጥሮ ወደ ሥራ ከገባ አራት ዓመታት ተቆጥረዋል። የክፍለ ከተማው መደራጀት ዋና ዓላማ ደግሞ የአገልግሎት ተደራሽነትና የማስተዳደር አቅምን በማጎልበት ለከተማው ነዋሪዎች ሚዛናዊ በሆነ ርቀት አገልግሎት መስጠት ነው። ይሁን እንጂ በክፍለ ከተማው አሁን ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ በተለይም በመሬት ነክ አገልግሎት ላይ በሕብረተሰቡ ዘንድ ቅሬታዎች እየተነሳበት መሆኑ ይነገራል።**

**እኛም በዛሬው የተጠየቅ ዓምዳችን የክፍለ ከተማውን እውን መሆን ተከትሎ የታዩ ለውጦች፤ የተገኙ ስኬቶችና ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎች ላይ በማተኮር፤ የሕዝቡን ጥያቄና ቅሬታ ማዕከል በማድረግ ችግሮችን ለመፍታት ምን እየሰራ ነው? የሚለውን ማዕከላዊ ጉዳይ በመያዝ፤ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ ከሆኑት አቶ ታረቀኝ ገመቹ ጋር ቆይታ አድርገናል። መልካም ምንባብ፡**

**አዲስ ዘመን፡- ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ዛሬ ላይ በሕዝብ ዘንድ በመልካምም በችግርም ስሙ ይነሳል። እርሶ ደግሞ በቅርቡ የክ/ከተማው ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆነው ተሹመዋል። የዚህ ክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈጻሚ መሆንዎ ምን ስሜት ፈጠረብዎት?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ይህ ለእኔ አዲስ አይደለም። የክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስጻሚ ስሆን ይህ አራተኛ ክፍለ ከተማዬ ነው። በልደታ፣ ቂርቆስና የካ ክፍለ ከተሞች በዋና ስራ አስፈጻሚነት መርቻለሁ። ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ስመጣ የስራ ጫና እንዳለ በተለይም አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ያሉ ችግሮች እንዳሉ ስሰማ ነበር።

ስለዚህ ከመምጣቴ በፊት አገልግሎት አሰጣጡ ላይ እንዴት አድርጌ አስተካክላለሁ የሚል ሀሳብ ከመፈጠሩ በስተቀር፤ ከአመራሩ፣ ከሰራተኛውና ከሕዝቡ ጋር ተቀራርቤ ለመስራት ችግር ስለሌለብኝ ብዙ ፍራቻ አልገጠመኝም። ግን ያሉ ችግሮች ውስብስብ ስለሆኑ እንዴት አድርጎ ማስተካከል ይቻላል የሚል ሀሳብ ነበረብኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በክፍለ ከተማው ያሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን በመቅረፍ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ምን ዕቅድ ነድፈዋል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ወደ ክፍለ ከተማው ስመጣ ምን ስራ ልሰራ እንደሚገባኝ በከፍተኛ አመራሮች በኩል ‹‹ኦረንቴሽን›› ተሰጥቶኛል። በዚህ መሰረት ዋናው ችግር መሬትና መሬት ላይ ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ነው። የመሬት አደረጃጀቱ ብዙ ችግር ያለበት ነው። ይህን ችግር ለመቅረፍ ስራዎች ተጀምረዋል።

ከሁሉም በፊት ከፋይል አደረጃጀት ጀምሮ መዝገብ ቤቱ ሲታይ ፋይሎች የሚገኙት ተበታትነው ነው። መዝገብ ቤቱ አራት ቦታ ላይ የሚገኝ ስለሆነ ለቁጥጥርና ለክትትል ምቹ አልነበረም። በዚህ ሳቢያም ባለቤት ስለሌለውና የሚቆጣጠር አካል ባለመኖሩ ፋይል ወስዶ የመቆየት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ስለሆነም በአሰራርና በአንዳንድ አደረጃጀቶች ላይ ያሉ ችግሮች እንዳሉ በክፍለ ከተማው ካሉ አመራሮች ጋር በካቢኔም በሌላ አመራሮች ጋርም በጠቅላላው ከመላ አመራሩ ጋር ያሉ ችግሮችን በተገቢው መንገድ ገምግመናል።

አንደኛው ችግር፤ ያሉ ፋይሎችን በደንብ ማየት፤ ስንት ፋይል አለው፤ ካሉ ፋይሎች ደግሞ በሕግ አግባብ የትኛው ትክክለኛ ነው፤ የትኛው ትክክለኛ አይደለም፤ የሚለው ከተማ አስተዳደሩ በራሱ ከአንድ ወር በፊት ጀምሮ እስካሁን ድረስ የማጥራት ስራ እየሰራ ነው። ይህም የመረጃ አደረጃጀቱን በማጥራት በኩል አጋዥ ተግባር ነው። ችግር ያለባቸውን ፋይሎችና ችግር የፈጠሩ ግለሰቦችን ጭምር ለይተው በማጠናቀቅ ላይ በመሆናቸው ክፍለ ከተማው በሚሰራው ስራ ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው።

ከአደረጃጀት አንጻር ከመዝገብ ቤት ጀምሮ የአግልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ እንዲሆንና ያልተፈለገ እንግልትና መመላለስ እንዳይኖር ለማድረግ የአስተዳደር መዋቅሩ ተስተካክሏል። ችግሮችን በመለየት መፍትሔ የማስቀመጥ ስራ እየተሰራ ነው። ያሉ አመራሮች አብዛኞቹ መስራት የሚፈልጉና አቅሙም ያላቸው ናቸው። በዚህም የአመራር ምደባ ማስተካከያ ሥራ ተሰርቷል።

**አዲስ ዘመን፡- እርሶም እንዳነሱት በክፍለ ከተማው ትልቁ ችግር ሕገ ወጥነት መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ረገድ በ2015 በጀት ዓመት ምን ሰራችሁ?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ሕገ ወጥነትን ከመከላከል አንጻር ብዙ ስራ ተሠርቷል። ከመሬት ወረራ ጋር በተገናኘ ወደ አንድ ሺ 299 ሕገወጦች ተለይተው ሙሉ በሙሉ እርምጃ በመውሰድ 53 ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ ገቢ ተደርጓል። ከመሬት ማስፋፋት አኳያ ደግሞ ካላቸው መሬት ጨምረው መሬታቸውን አስፋፍተው የያዙ 52 ሰዎች ተለይተው በተወሰደ ርምጃ አራት ሺ973 ካሬ ሜትር የሚሆን መሬት ተመልሷል። ከግንባታ አንጻር ደግሞ 495 ሰዎች ተለይተዋል።

ሕገ ወጥ የጎዳና ላይ ንግድ በተመለከተ ደግሞ 99 የሚሆኑ ሕገ ወጥ ደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት፣ 277 በሕገ ወጥ እንስሳት እርድ በተመሳሳይ እርምጃ ተወስዷል። በተወሰዱት እርምጃዎች በቅጣት ደረጃ አንድ ሚሊዮን 193ሺ 325 ብር በቅጣት ገቢ ተደርጓል። ሕገወጥ ሲገኝ እርምጃ ወስዶ ማስተካከል ከመሬት ወረራ፣ ማስፋፋት፣ ከሕገወጥ ግንባታ በሌሎች ነገሮች ላይ እርምጃ ተወስዶባቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ከወረዳ በብልሹ አሰራር ውስጥ የተገኘ አመራርም ሆነ ባለሙያ ወደ ክፍለ ከተማ የመመደብ ስራ ሲሰራ እንጂ እርምጃ ሲወሰድበት አይታም፤ ይህ ለብልሹ አሰራር በር እንደከፈተ ስለመሆኑ በሕብረተሰቡ ዘንድ ይነሳል፤ የእርስዎ ምላሽ ምንድን ነው?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** አመራር ሁለት ሚና አለው። የመጀመሪያው ለማረምና ለማስተካከል ራሱ ከሌብነትና ብልሹ አሰራር ነጻ መሆኑን ይጠይቃል። በሁለተኛ ደረጃ ችግር ውስጥ የገቡ ሰዎችን ለማረምና ለማስተካከል ኃላፊነት አለበት። አመራሩ ከተበላሸ ሁሉም ይበላሻል። ስለዚህ አመራሩን መልሶ ሲደራጅ ችግር ያለባቸው አመራሮች ምን ችግር እንዳለባቸው ተለይቷል። በተደረገው ልየታ መሰረት ብዙ አመራሮች ላይ እርምጃ ተወስዷል። የማሳደግ፣ ከቦታ ቦታ መቀየር ሳይሆን፤ ችግር ያለባቸው ከአመራርነት እንዲነሱ ተደርጓል።

ለምሳሌ ወረዳ 13 እና ወረዳ 06 ላይ ኦዲት ተደርጎ በብልሹ አሰራር ውስጥ የተገኙ ብዙ አመራሮች በግምገማ እንዲነሱ ተደርጓል። ሌሎች ወረዳዎች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ተወስዷል። አመራሩ በአመራሩ ላይ ባነሳው ሀሳብ ልክ፤ ከሕብረተሰቡ በተገኘው ጥቆማ መሰረት ተደርጎ 26 ሰዎች ከአመራርት እንዲነሱ ተደርጓል። ይህ ሲባል ግን የቀሩ አመራሮች ሁሉም ንጹህ ናቸው ማለት አይቻልም። ይህ በቀጣይም ብዙ ስራ የሚጠይቅ ነው።

እስካሁን ድረስ በሕዝብና በአመራር በሌብነትና ብልሹ አሰራር ውስጥ ገብተዋል ተብለው የተለዩ አመራሮችን ከአመራርነት እንዲወጡ ተደርጓል። በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል። ለምሳሌ፣ በመቶ ቀን ዕቅድ ውስጥ ሕገ ወጥነትን ለመከላከል የመሬት ወረራን ከመከላከል አንጻር በጸጥታ አስተዳደር የሚመራ ቡድን የተቋቋመ ሲሆን፤ በየሳምንቱ ዋና ስራ አስፈጻሚው በተገኘበት ይገመገማል። ሰባት የሚሆኑ ግብረ ኃይሎች ተቋቁመዋል። ለኑሮ ውድነትን መፍትሄ የሚሹ፤ ፕሮጀክቶችን የተመለከቱ ብልሹ አሰራርና ሌብነት የመልካም አስተዳደር ችግሮች የራሱ የሆነ ኮሚቴ ተደራጅቷል።

**አዲስ ዘመን፡- አመራር ቦታ በማቀያየር ብቻ በሕብረተሰቡ ዘንድ የሚነሱ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን መፍታት ይቻላል ብለው ያስባሉ?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ችግሮቹን ለማቃለል በዋናነት አመራር መቀየር ሳይሆን፣ አመለካከቱን መለወጥ ላይ መስራት ነው። ባለሙያውንና አመራሩን በማደራጀትና በማቀናጀት በተልዕኮ ስምሪት በመስጠት እየገመገሙ ችግር ካለ ችግሩን በማረም ካልተስተካከለ ሰውን በማንሳትና ሰውን በማምጣት ብዙም ለውጥ ማምጣት አይቻልም።

ዋናው የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ነው። የመሬት አገልግሎት አደረጃጀቱ ችግር እንዳለ ሆኖ ዋናው ጉዳይ ከእጅ ንክኪ ነጻ እንዲሆን ማድረግ ነው። ማንዋል በሆነው አሰራር ከፍተኛ ችግር የሆነው ፋይል መደበቅ፤ ለፋይል ማውጫ እጅ መንሻ መጠየቅ እና መሰል ችግሮች ስላሉ ወደ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ለማምጣት ሁሉም መረጃ ሙሉ በሙሉ ስካን የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁንም ከአመራሩ ጋር ተያይዞ በሕብረተሰቡ ዘንድ ቅሬታዎች ይነሳሉ፤ አመራሩ ችግሩን በልኩ ተገንዝቦ ለማስተካከል ምን ሰርቷል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ችግሮችን ለመፍታት ዋናው ጉዳይ አመለካከት ነው። ከዚህ ችግር ውስጥ እንድንገባ ያደረገን የአመለካከት ችግር ነው። ሰው አገልጋይ ነኝ፤ ነጻ አገልግሎት እሰጣለው ብሎ በቅንንት ወደ ስራ ከገባ ምንም ችግር የለውም። ስለዚህ የመሬት ልማት አመራሮችን እንዲስተካከሉ ተደርጓል።

ከዘርፎች ቀጥሎ ቡድን መሪዎች አሉ፤ ቡድን መሪዎችን ከተማ አስተዳደሩ ለማስተካከል ኦዲት እያደረገ ነው። የኦዲት ግኝት ሪፖርቱ እየወጣ ስለሆነ ችግር ያለባቸው ሰዎችንና ችግር የሌለባቸውን ነጥረው እንዲወጡ ተደርጓል። እናም ችግር ያለባቸው ከመሬት ጽሕፈት ቤት እንዲወጡ የሚደረጉ ሲሆን፤ የሌለባቸው ደግሞ ይቀጥላሉ።

**አዲስ ዘመን፡- አገልግሎቱን በማዘመን በኦንላይን ለመስጠት የባለሙያውና የአመራሩ ቁርጠኝነት እስከምን ድረስ ነው?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ዋናው የአመለካከት ችግር ስለሆነ ባለሙያዎች የመስራት ፍላጎታቸው በጣም አናሳ ነው። አመራሩም ይህን በደንብ በመያዝ በማንዋል አገልግሎት መስጠት አትችሉም ብሎ አቋም ይዞ ማስተካከል ላይ ችግር ነበር። ከመጀመሪያም ሲስተሙ ከተመረቀ ጀምሮ ስካን ሆኖ ለአገልግሎት ብቁ የሆኑ ፋይሎች አሉ። ባለው በተነሳሽነት አገልግሎት መስጠት ቢጀምር የቀረውም በተፈለገው መንገድ ተጠናቆ ሙሉ በሙሉ ወደ አገልግሎት መግባት ይቻል ነበር። ነገር ግን ከፍላጎት ማጣት ስለመጣ ችግሩ ውስብስብ እንዲሆንና ለሌብነትና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ እንዲሆን በር ከፍቷል።

መረጃዎችን ስካን በማድረግ ሙሉ በሙሉ ወደ ሲስተም እንዲገባና በኦንላይን አገልግሎት መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ለመፍጠር እየተሰራ ሲሆን፤ ይህም ሌብነትን ይከላከላል። አገልግሎት ፈላጊውም ፋይል ጠፋ ከሚለው አላስፈላጊ እንግልትና ወጭ እንዲድን ያደርጋል። ከዚህም በላይ ዋና ስራ አስፈጻሚውን ጨምሮ ሌሎች አመራሮች ባለሙያ ምን እየሰራ እንደሆነ ለመከታተል ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።

ለምሳሌ፣ በክፍለ ከተማው አንዱ ችግር የሆነውን የመሬትና መሬት ነክ ጉዳይ ለመፍታት ዋናውና አንዱ መፍትሔ ሁሉም የመሬት ነክ አገልግሎት ወደ ሲስተም ማስገባት ነው ብለን እየሰራን ነው። እስካሁንም ከእጅ ንክኪ የጸዳ እንዲሆንና ያለው ፋይል ስንት እንደሆነ ልየታ ስራ ተሰርቷል። ሲስተሙ በተመረቀበት ወቅትም ወደ 37ሺህ የሚሆን ፋይል ስካን ተደርጎ ገብቷል።

**አዲስ ዘመን፡- አገልግሎት አሰጣጡን ያዘመናል፤ ሌብነትና ብልሹ አሰራርን ይቀርፋል ተብሎ ታስቦ እየተሰራበት ያለው የኦንላይ አገልግሎት ችግሩን ምን ያህል ቀርፏል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** መረጃዎች ስካን ተደርገው ለኦንላይን አገልግሎት መዘጋጀታቸው ለስራ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል



**አመራር ሁለት ሚና አለው። የመጀመሪያው ለማረምና ለማስተካከል ራሱ ከሌብነትና ብልሹ አሠራር ነጻ መሆኑን ይጠይቃል። በሁለተኛ ደረጃ ችግር ውስጥ የገቡ ሰዎችን ለማረምና ለማስተካከል ኃላፊነት አለበት**

# ተጠየቅ

# «ሌብነትና ብልሹ አሠራር ውስጥ ገብተዋል ተብለው ...

**ከገጽ 6 የዞረ**

ነገር ግን ዋናው ችግር የነበረው የማስቀጠሉ ጉዳይ ነው። ያለውን ፋይል ለይቶ ምን ያህል ፋይል እንዳለ ማሳወቅ አለመቻልም ሌላው ችግር ነው። ለምሳሌ፣ ሲጠየቅ የተወሰነው 54ሺ ሌላው ደግሞ 64ሺ ይላል። ሆኖም ይሄ ሰበብ ነው እንጂ የሚደበቅ ነገር የለም።

ከዛ ውጪ ለዚህ ፍላጎት አለማሳየት ባለሙያው ጋር ያሉ ችሮች ናቸው። ሆኖም አሁን ዋናውን ችግር ይቀርፋል ተብሎ የሚታሰበው ያለው የፋይል ብዛት ታውቋል። አዲስ ሲገባም እንዴት እንደሚገባ አሰራር ይበጃል። ፋይሉ ከታወቀ ደግሞ በውጭ ፋይል ማደራጀትና እንደፈለጉ ማስገባትና ማስወጣት አይቻልም። ባለቤት ይኖረዋል፤ በመሆኑም ሲስተሙ በዚያ ደረጃ በአገልግሎት አሰጣጡ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮችን ይቀርፋል።

**አዲስ ዘመን፡- መረጃው ሙሉ በሙሉ በኦንላይን ሲሰጥ በመሬት ላይ እየተስተዋለ ያለውን ሌብነት መቅረፍ ያስችላል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ኦንላይንም ቢሆን የሚሰራው በሰው ነው። ስለሆነም ሰው አመለካከቱ ካልተቀየረ ሁሉም ነገር በአንድ ጊዜ አይስተካከልም። ነገር ግን የተጋላጭነት መጠኑን በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል። ለምሳሌ፣ ፋይል ጠፋ የሚባል ወሬ አይሰራም። ለክትትልም ምቹ ስለሆነ አመራሩ የሚሰጠው አገልግሎት ኦንላይን ላይ ስለሚከታተል የቱ ጋር ችግር እንዳለ መለየት ይቻላል። ለማስተካከልና ለመገምገም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

**አዲስ ዘመን፡- በክፍለ ከተማው በርካታ ቤቶች ሕጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የላቸውም፤ በዚህ ሳቢያም ለብልሹ አሰራር በር ከፍቷል ተብሎ ይነሳል። ቤቶቹን መመሪያንና ሕግን በተከተለ አግባብ ከማስተዳደር አንጻር ምን ታቅዷል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** የመሬት አገልግሎት አካባቢ ችግሮች አሉ። ነገር ግን አሁን ላይ ሁሉም አግባብነት ያለውና ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ መረጃ እንዲኖር ከማድረግ አንጻር መለየት አስፈላጊ ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ የጣሪያና ግድግዳ ግብር ለማስከፈል እንኳን ምቹ ሁኔታ አይፈጥርም። አሁን ላይ ያለውን ችግር ለማስተካከል በዕቅድ ተይዟል። የአርሶ አደሮችም ተለክቶ ካርታ ያገኙ አሉ። ተለክቶ ደግሞ ከለውጡ በፊት ካሳ በልተዋል ተብሎ እየተጣራ ያለም አለ። በዚህም የካሳ ልዩነት መክፈል ያለበትን ለመክፈል ሕጋዊ እንዲሆኑ እተሰራ ነው።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ልኬት ያልወሰዱ እንዲወስዱ፤ ልኬት ወስደው ሁሉንም ነገር ጨርሰው በካሳ አከፋፈል ላይ ተከፍሏል ተብለው የቆዩም የወሰዱትን ወደ ሕግ አግባብ የማስገባት ስራ ይሰራል። ይህ ሲሆን ሕገ ወጥነትን ይከላከላል፤ የመሬት ወረራን ተጋላጭነም ይቀንሳል። ይህን ለማድረግ ከተማ ግብርና እና መሬት ጽህፈት ቤት በቅንጅት እየሰሩ ነው። ካርታ የሌላቸው ግለሰቦች የራሳቸው ይዞታ ከሆነና ይዞታቸው ነው ተብሎ ከተረጋገጠ ካርታ የሚሰጥበት ሁኔታ ይፈጠራል። በዚህ መልኩ የሕዝብ አንገብጋቢ ጥያቄ ያለባቸው ቦታዎች እየተመለሱ ይሄዳሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ክፍለ ከተማው በርካታ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ያሉበት እንደመሆኑ የመብራት፣ የውሃና የመንገድ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ከመፍታት አንጻር ምን ታስባል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** የጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ የመንገድ፤ የውሃና የመብራት ብዙ ጥያቄዎች አሏቸው። ችግሩን ለመፍታት ከመንገዶች ባለስልጣና ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጋር ውይይት ተደርጓል። ያስቸገሩን በጋራ መኖሪያ ቤቶች ሳይቶች ውስጥ አርሶ አደሮች እርሻ እያረሱ፤ ካሳ ይገባናል የሚል ጥያቄ እያቀረቡ መሆኑ ነው።

ይህም የተፈጠረው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሳይት ላይ መሬት ፆም ማደር የለበትም የሚለው ሀሳብ ሲተገበር ተመልሰው ገብተው ማረስ የጀመሩ አርሶ አደሮች በጊዜ ቆይታ የባለቤትነት ጥያቄ ፍላጎት የመጣ ሲሆን፤ አብዛኛዎቹ ቦታዎች በመነጋገርና በመተማመን እየወጡ ነው። መንገድ እንዲሰራ ከመንገዶች ባለስልጣን ጋር በተደረገው ውይይት መሰረት መንገዶች እየተሰሩ ነው። በቀጣይ ይህን የማወያየትና የመተግበር ስራ ከስራ አስፈጻሚው የሚጠበቅ ነው።

አንዴ ካሳ ተቀብለዋል፤ መሬቱ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሳይት በመሆኑ ሁለተኛ ካሳ የሚከፈልበት አግባብ የለም። በሌላ በኩልም አንዳንድ ኮንትራክተሮች ያለመስራት ፍላጎት አላቸው። መንገዶች ባለስልጣንና ክፍለ ከተማው በማያውቀው ሁኔታ አርሶ አደሮችን የእኔ ነው በልና ከዚህ እንወጣለን የሚል ሀሳብ ያነሳሉ። ይህ ችግር እንዳይደገም



ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ላይ እንደ ችግር የሚነሳው መሬት ነው። የመሬት ጉዳይን ለማስተካከል ደግሞ ከከንቲባዋ ጀምሮ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ተቋራጮች ላይ እርምጃ እንዲወስድና እንዲስተካከሉ መግባባት ላይ ተደርሷል። ያሉ ችግሮችን ሁሉ በሚገባው ልክ ችግሩን ተረድቶ የራሱን የቤት ስራ በመስራት እንዲቀረፍ የጋራ መግባባት ላይ የተመሰረተ ስራ እንዲሰራ ማድረግ ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ሕገ ወጥነት ተስፋፍቷል፤ የወንጀለኞች መደበቂያ እየሆነ ነው የሚል ሀሳብ ይነሳልና እርሶ እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ይህ ጉዳይ በእኛ የሚጣራ አይደለም። የጋራ መኖሪያ ቤቶች ቤቶችን የሚሰጠው የከተማ አስተዳደሩ ቤቶች ነው። ሕገ ወጦች የሉም ማለት አይደለም። ከወንጀል አንጻር ግምገማ ተደርጎ በአካባቢው ባሉት ሁለት ሳይቶች ላይ የስርቆት ወንጀል መኖሩ ታውቋል። ስርቆቱ ከውጭ ነው ከውስጥ የሚለውን ከዛው ያሉ ጠባቂዎች ስላሉ እነሱ እያሉ ለምን ወንጀሉ እንደሚፈጸም መገምገም ያስፈልጋል።

ከውጭ ከሆነ ደግሞ እንዴት መግባት ቻሉ የሚለውን ወረዳ አመራሮች ባሉበት ተገምግሟል። በዚህም በተለይም በአካባቢው በጫኝ አውራጅ ላይ የሚስተዋል ከአቅም በላይ የመጠየቅ እንቅስቃሴ ላይ ሰፊ እርምጃ ተወስዷል። ይህን ስራ የሚሰሩትን ወረዳ አደራጅቶ ስላስገባ ኃላፊነቱን ወስዷል።

የጸጥታ ስራውን የክፍለ ከተማው ፖሊስ መምሪያና ሰላምና ጸጥታ ከወረዳዎች ጋር ኃላፊነቱን ወስዷል። የመሰረተ ልማት እንደ ምክንያት ከተነሳም፣ ወሰን ከተከበረላቸው በኋላ በቶሎ መንገዱን የመክፈትና የመስራት ኃላፊነት የመንገዶች ባለስልጣን ነው። ከዛ ውጪ በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ያሉ ስርቆቶችን ቤቶች እንዲመለከቱና ራሳቸው እንዲያስተካክሉ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል።

**አዲስ ዘመን፡- ለቤተ እምነቶች የሚውሉ ግንባታዎች መበራከታቸው ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን አመራሩ እንዴት ይመለከተዋል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ወስኖ ለሁሉም ቤተ ዕምነቶች ሕጋዊ ቦታ ተሰጥቷል። ሆኖም ከተሰጣቸው መሬት አልፎ የማጠር ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ነው። ይህን ችግር ለማስተካከል ስራ የተጀመረ ሲሆን እስካሁን ሁለት ቦታዎች አራት ሺህ ካሬ ሜትር የተሰጠው አንድ ቤተ ዕምነት ስምንት ሺ ካሬ ሜትር ጨምሮ አጥሮ ተገኝቶ በተቋቋመው ግብረ ኃይል እርምጃ ተወስዶበታል።

ሆኖም በመሬት ከተሰጣቸው በኋላ እላፊ መሬት ለማግኘት አንድም ከአርሶ አደሩ ጋር በመነጋገር ሌላም በጉልበት ያጥራሉ። ቤተ ዕምነትን ሽፋን በማድረግ ግልጽ የሆነ የመሬት ወረራ ፍላጎቶች አሉ። ማንኛውም ግለሰብም ይሁን የዕምነት ተቋም ከሕግ በላይ ሊሆን ስለማይችል ሕገ ወጥነትን በምንም መልኩ አንታገስም።

በዚህ ረገድ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሰላም ሰራዊቱ በከፍተኛ ሁኔታ ተጠናክሮ እየተሰራ ነው። ከመስከረም ወር ጀምሮ በተደራጀ መልኩ በመሰራቱ ሕገ ወጥነት የለም። ደንብ ማስከበር ብሎክን መሰረት ያደረገ ስምሪት ወስዶ እየሰራ ሲሆን፤ በተመደቡበት አካባቢ ችግር ተፈጥሮ ከተገኘ ተጠያቂ ይሆናሉ። በተጨማሪም በየብሎኮች የወረዳ አመራር ምደባ ተደርጎ ክትትል ያደርጋሉ። ማንኛውም ግለሰብ ከምንም ተነስቶ በሕገ ወጥ መንገድ መሬት አያጥርም፤ አንዳንድ ነገሮች ከጀርባው ስላሉ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ክፍለ ከተማው ከሪል ስቴት አልሚዎችና ከአንዳንድ ድርጅቶች ጋር ከካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ አርሶ አድሮች ክስ ውስጥ መሆናቸውን አስተዳደሩ ያውቃል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** በአብዛኛዎቹ ላይ እውቅናው ስለሌለኝ ሀሳብ አልሰጥበትም። እስካሁን ወደ እኔ የመጡ ሰዎችም የሉም። አርሶ አደሮች አካባቢ ያለው አንዳንድ ጉዳዮች አብዛኛው ቦታው ለልማት ሲፈለግ የካሳ አከፋፈሉ ሁኔታና የገንዘብ ችግር ሊኖር ስለሚችል የመተማመኛ ደብዳቤ ይሰጣል። ሂደቱ ካለቀ በኋላ ካሳ ይከፈላል። ጥያቄው እውነትም ውሸትም ሊሆን ይችላል። እውነት ከሆነ መጥቶ መጠየቅ ይችላሉ። መሬታቸው ያለምንም ካሳና ምትክ መወሰድ የለበትም። መገፋት ከሆነ ከለውጡ በፊት የተገፋት በቂ ነው።

ያልተከፈለ ካሳ ካለ በሕግ አግባቡ ጠይቆ እንዲከፈል እናደርጋለን። ሪል ስቴት አልሚዎች ጋር የመካሰስና የመጋጨት ሁኔታ አለ። ይህም ሪልስቴት አልሚዎቹ አልፈው የመውሰድ ፍላጎትና በቂ ካሳ ያለመክፍል ችግር ሁኔታ አለ። ከአያት ሪልስቴት ጋር ያለውን ለመፍታት ኮሚቴ ተደራጅቶ ችግሩ የቱ ጋር እንደሆነ ለመለየት ወደ ስራ ተገብቷል። ችግሮች የአርሶ አደሩም ይሁን የሪል ስቴቱ ማስተካከል ኃላፊነት ያለበት የመንግስት ስለሆነ የካሳ ጉዳይን በአሰራሩና በሕግ አግባብ የሚመለስ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በክፍለ ከተማው እየተከናወነ ሳለው የጫካ ፕሮጀክት የልማት ተነሺዎች አርሷደሮች ከካሳ ክፍያና ከልማቱ ተጠቃሚነት አኳያ ቅሬታ ያነሳሉ፤ ይህን በተገቢው ሁኔታ ከማስተናገድ አንጻር ምን ይላሉ?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** 166 የሚሆኑ አርሶ አደርና የአርሶ አደር ልጆች ጫካ ፕሮጀክት ውስጥ ገብተዋል። ጫካ ፕሮጀክቱ ብዙ አርሶ አደሮችን ገፊ ሳይሆን አቃፊ ነው። ይህን የምንልበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። አንደኛ በቂ የሆነ ካሳ ነው የሚከፈለው። ምትክ ቦታም ይሠጣቸዋል። ሦስተኛ ደግሞ የጫኝና አውራጅ ሌሎች ነገሮችም የአንድና የሁለት ዓመት ኪራይ ይሠጣል። እስካሁን ድረስ 35 ሰዎች መጥተው አልወሰዱም እንጂ ካሳ ተሠርቶ ተቀምጦላቸዋል።

ምትክ ቦታን በሚመለከትም ከዚህ በፊት ታይቶ ነበር። አንድ አካባቢ ቢሆኑ፤ ማሕበራዊ መሠረታቸው እንዳይበታተን ተመልሳችሁ እዩ ብየ ነበር። በዚህ መሰረት አንድ ቦታ ተደራጅቶላቸዋል። ቦታቸውም ይሰጣቸዋል። ይህንንም በቶሎ እናስተካክላለን። በጥቅሉም የምትክ ቦታና ካሳ ጉዳይ ላይ ተማምነው ፈርመዋል። በመግባባት ነው ሁሉም ነገር ያለቀው። የመዘግየት ችግር ብቻ ነው ያለው። ይህንንም አፋጥነን ወደ ስራ አስገብተናል።

**አዲስ ዘመን፡- ክፍለ ከተማው ብዙ ጊዜ ስሙ በጥሩ አይነሳም። ስሙን ቀይሮ ሞዴል ክፍለከተማ ለማድረግ ከማን ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ላይ እንደ ችግር የሚነሳው መሬት ነው። የመሬት ጉዳይን ለማስተካከል ደግሞ ከከንቲባዋ ጀምሮ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው። ሪፎርም የማድረግ ስራዎችም ተጀምረዋል። ጉዳዩ የለሚ ኩራ ብቻ ስላልሆነም ከተማ አቀፍ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ናቸው። በዚህም እንደ ክፍለ ከተማ እናስተካክላለን የሚል እምነት አለኝ። ከዚህ ውጪ ክፍለ ከተማው በትምህርት፤ በጤናው ጉዳይ፤ በሕብረተሰብ ተሳትፎ፤ ከፕሮጀክት አፈጻጸም አኳያ በጣም ጥሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የክፍለ ከተማው ሌላኛው ችግር ለሚዲያው ክፍት አለመሆን ነው። በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ትክክል ነው። በክፍለከተማው አንዱ የመልካም አስተዳደር ችግር ተብሎ ከተገመገመው ውስጥ የኮሙኒኬሽን ችግር ይገኝበታል። በውስጣችንም ማለት ነው። እኛም የራሳችን ሚዲያ አለን፤ የፓርቲ ሚዲያም አለ። አመራሩም በራሱ ኮሚኒኬተር መሆን አለበት። ከዚያም በተጨማሪ ለሚዲያው ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና ያለን መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው። ያለን ዳተኝነት ማቆምም ይገባል።

መስራት እንጂ የተሰራውን ማሳወቅ ላይ በጣም ችግር አለብን። ለምሳሌ አመራሮች የተለያዩ ክልሎች ላይ ሄደው ጉብኝት እያደረጉ ነው። ላልሰማው ብናሰማ የተሰሩ ስራዎች እንዲታዩ ይሆናሉ፤ ሕዝቡ ውስጥ ተስፋ ይኖራል።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ሳደረጉት ቆይታ እናመሰግናለን።**

**አቶ ታረቀኝ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ክልሉ ከ33 ሺህ ቶን በላይ ቡና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ አቅዷል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡-በ2016 የምርት ዘመን ከ33 ሺህ ቶን በላይ ቡና ለውጪ ገበያ ለማቅረብ አቅዶ እየሠራ መሆኑን የሲዳማ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

በክልሉ የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ መምሩ ሞኬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከ33 ሺህ ቶን በላይ ቡና ማቅረብ የሚያስችል ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።

በበጀት ዓመቱ 10 ሺህ ሔክታር መሬት በቡና ተክል ለመሸፈን የታቀደ ሲሆን፤ ከ30 ሚሊዮን በላይ የቡና ችግኝ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

አዲስ የተዘጋጁት የቡና ችግኞችን እንደአየሩ ፀባይ በዓመቱ አጋማሽ ወይንም በሚያዝያ ወር ላይ መትከል እንደሚጀመር አስረድተዋል፡፡

አሁን ያለው የክልሉ የቡና ማሳ ሽፋን 164 ሺህ ሄክታር መሬት ሲሆን፤ በዘንድሮው በጀት ዓመት ወደ 174 ሺህ ሄክታር መሬት ለማድረስ ታቅዷል ብለዋል፡፡

በክልሉ ከቡና ምርት ጋር ተያይዞ በአንድ ሔክታር ከ10 ኩንታል በላይ የቡና ምርት እንደሚገኝ አመላክተው፤ ለቡና ማሳ የሚውል ሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ቶን ኮምፖስት መዘጋጀቱን ተናግረዋል።

በክልሉ ከሚገኘው 164 ሺህ ሄክታር መሬት ቡና 134 ሺህ የቡና ዛፎች ምርት እየሰጡ መሆኑን ጠቁመዋል።

ምርታማነትን ለማሳደግ ያረጁ የቡና ተክሎችን የመተካት፣ የቡናን ተክል የመጎንደልና የመንከባከብ ሥራ በማከናወን ምርታማነቱን ለመጨመር ጥረት እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

በክልሉ የሚገኙ 74ቱ የቡና ግብይት ማዕከላት ወደሥራ መግባታቸውን አመላክተው፤ በተጨማሪ 142 የመገበያያ ስፍራዎችን ወደሥራ ለማስገባት የቅድመ ዝግጅት ሥራ መጠናቀቁን አስረድተዋል።

በአጠቃላይ በክልሉ 388 ስፍራዎች ላይ የቡና ግብይት ለማከናወን የሚያስችል ድጋፍ የሚሰጥ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ በመሥራት ላይ ይገኛል ብለዋል።

በ2015 በጀት ዓመት ከክልሉ የቡና ምርት 31 ሺህ ቶን ቡና ለውጪ ገበያ መቅረቡን አቶ መምሩ አስታውሰዋል።



# ከ41 ሚሊዮን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፤ በቆዳ ዘርፉ ባሉበት ችግሮች ምክንያት በሀገር አቀፍ ደረጃ በዓመት ከሚገኘው 41 ሚሊዮን በላይ የቆዳና ሌጦ ምርት ግማሹ ብቻ አገልግሎት ላይ ይውላል። በዚህ የተነሳም ሀገሪቱ ከቆዳ ዘርፍ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ እያገኘች አይደለም።


የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አናሳ መሆን፣ የዓለም የቆዳ ምርቶች ገበያ መቀዛቀዝ፣ የመኳኳዣ እጥረት፣ የጥሬ ቆዳ አሰባሰብ ችግር፣ ምርቶች የሚቀርቡበት ሰፊ ገበያ አለመኖርና የግብዓት አቅርቦት እጥረት ዋነኛ የዘርፉ ማነቆዎች መሆናቸውን አቶ መላኩ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ ከ165 ሚሊዮን በላይ የቀንድ ከብት ሀብት ቢኖራትም የሚገኘው የቆዳና ሌጦ ምርት ዝቀተኛ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ችግሩን ለመፍታት ለ10 ዓመታት የሚተገበር የቆዳ ልማት ስትራቴጂ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

በስትራቴጂው መሠረት በዘርፉ ቀጣይነት ያለው ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ለማሻሻል፣ የጥሬ ቆዳ አቅርቦትና ጥራትን ለማሳደግና ሌሎች ሀገራት በቆዳ ውጤቶች ያደጉባቸውን መንገዶች ለመቅሰም ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

በተጨማሪ የቆዳና ቆዳ ውጤት መዳረሻ ሀገራትን ማሳደግ፣ የሀገር ውስጥ ገበያን መጠቀም፣ ከውጭ የሚገቡ ኬሚካሎችን በሀገር ውስጥ ማምረትና ሌሎች የመፍትሔ ሀሳቦች በስትራቴጂው የሚተገበሩ መሆናቸውን አብራርተዋል።

የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል ሥራ አስኪያጅ አቶ መሐመድ ሁሴን በበኩላቸው፤



በዘርፉ የሚስተዋሉ ማነቆዎችን ለመፍታት ከ2016 እስከ 2025 ዓ.ም በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የሚተገበር የቆዳ ልማት ስትራቴጂ መነደፉን ገልጸዋል።

የጥሬ ቆዳ ጥራት ችግርን ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል ያሉት አቶ መሐመድ፤ በእርድ ወቅትና ከእርድ በኋላ የሚፈጠሩ የጥራት መጓደሎችን ለማስቀረት ለማኅበረሰቡ ግንዛቤ የመፍጠር ፣ ለቆዳ ምርት ግብዓት የሚውለውን የጨው አቅርቦትን የማሳደግ እና ቆዳ ለሚያዘጋጁ አካላት ሥልጠና መስጠት ከሚሠሩት ሥራዎች መካከል ዋነኞቹ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

አምራች ፋብሪካዎች የተለያዩ ኬሚካሎችን በአብዛኛው ከውጭ ሀገራት በማስመጣት እንደሚጠቀሙ ገልጸው፤ ግብዓቶቹን በሀገር ውስጥ ለማምረት ጥረት እንደሚደረግ አመላክተዋል።

ማምረት ካቆሙት የቆዳ ፋብሪካዎች የተወሰኑት ወደ ሥራ ተመልሰው የሀገር ውስጥ ገበያ ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከቱ ይገኛል ያሉት አቶ መሐመድ፤ የሌሎች ፋብሪካዎችንም ችግር ደረጃ በደረጃ በመፍታት ሙሉ በሙሉ ወደ ምርት እንዲገቡና በሀገር ውስጥና በውጭ ገበያዎች በስፋት እንዲሳተፉ ጥረት እንደሚደረግ አስታውቀዋል።

የቆዳ ጫማ፣ የቆዳ ጓንትና ቦርሳ በዋነኛነት አምራች ፋብሪካዎች ወደ ውጭ ሀገራት የሚልኳቸው ምርቶች መሆናቸውን ገልጸው፤ ቻይና፣ ሕንድ፣ አሜሪካ፣ ጣሊያን፣ ታይላንድ፣ ኢንዶኖዢያና ቬትናም ዋናዋና የምርት መዳረሻ ሀገራት ናቸው፤ በቀጣይ መዳረሻዎቹን የማሳደግ ሥራ እንደሚከናወን ጠቁመዋል።

# “ኢትዮጵያ በስንዴ ምርት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ወደ አራት ቶን ማሳደግ መቻሏ የሚደነቅ ነው ሲሉም የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት አኪንውሚ አዴሲና (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ እ.አ.አ በ2023 የምርት ዘመን አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ስንዴ ይሰበሰባል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

እ.አ.አ. በ2018/19 የምርት ዘመን በ5ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ሲለማ የነበረውን የስንዴ ምርት እ.አ.አ በ2022/23 የምርት ዘመን ወደ አንድ ነጥብ 4 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ማሳደግ መቻሉን አስታውሰዋል።

የአፍሪካ ልማት ባንክ የግብርና ቴክኖሎጂ ትራንስፎርሜሽን ኢኒሼቲቭ የኢትዮጵያን በስንዴ ምርት ራስን የመቻል ጥረትን ለማገዝ ከ100 ሺህ ቶን በላይ ድርቅን ተቋቁሞ ምርት መስጠት የሚችል የምርጥ ዘር ማቅረቡን ጠቁመዋል።

በውይይቱ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳሕለወርቅ ዘውዴን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራት ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና የአፍሪካ ልማት ባንክ የሥራ አመራሮች ተገኝተዋል፡፡ ፕሬዚዳንት ሳሕለወርቅ ዘውዴ ከመርሐ ግብሩ ጎን ለጎን በርካታ ውይይቶችንም አድርገዋል፡፡

የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት አኪንውሚ አዴሲና ከዚህ ቀደም ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጋር በአዲስ አበባ ከተማ የተሠሩ የሪፎርም ሥራዎችን መጎብኘታቸው የሚታወስ ነው።

# የፎቶ ዓውደ ርዕዩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባሕልና ኪነ ጥበብ እንዲሁም የቱሪዝም ቦታዎችን የሚያስቃኙ ፎቶዎች በዓውደ ርዕዩ ቀርበዋል ያሉት ጄንጊዝ፤ የዓውደ ርዕዩ ይዘት የፎቶ ዶክመንተሪን ባሕሪ የተላበሰ መሆኑን ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎችና አስጎብኚ ድርጅቶች በየዓመቱ ቁጥራቸው ከፍ እያለ መጥቷል። ይህም በርካታ ቱሪስቶችን ወደ ሀገሪቱ እንዲመጡ እያደረገ ነው ያሉት ጄንጊዝ፤ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለች ሀገር መሆኗን የሚያሳዩ በርካታ ሥራዎች መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

በአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሃፍታይ ገብረእግዚአብሔር በበኩላቸው፤ ዓውደ ርዕዩ የከተማዋን ቱሪዝም መዳረሻ ለማሳየት የተዘጋጀ ነው። በፎቶ ዓውደ ርዕዩ የስፖርትና የጤና ቱሪዝም ድሮና ዘንድሮ እንዲሁም የከተማዋ ቱሪዝም ምን ለውጥ እንዳመጣ የሚያሳዩ ፎቶዎች ለዕይታ የቀረቡበት ነው ብለዋል።

በዓውደ ርዕዩ የቀረቡት ፎቶዎች ታሪክና ቅርስ ሆነው የሚያገለግሉ በመሆናቸው የሚመጣው ትውልድ ከተማዋ ከየት ወዴት እንደተጓዘች እንዲገነዘብ እና ምን መሥራት እንዳለበት የሚያሳውቁ ናቸው ያሉት አቶ ሃፍታይ፤ ከ80 በላይ አምባሳደሮች ዓውደ ርዕዩን ጎብኝተዋል። በዚህም ከተማዋ ያላትን የቱሪዝም ሀብት በጥቂቱ እንዲገነዘቡ አድርጓል ብለዋል።

ይህም አምባሳደሮቹ በዓውደ ርዕዩ የተመለከቱትን ፎቶዎች በአካል ሄደው እንዲጎበኙ ያደርጋል ያሉት አቶ ሃፍታይ፤ ዓውደ ርዕዩ ስኬታማ እና ይበል የሚያሰኝ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሪፎርም ሥራው በርካታ የፎቶ ዓውደ ርዕዮችን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች አዘጋጅቶ ለዕይታ ክፍት አድርጓል ያሉት ደግሞ የድርጅቱ የይዘት ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ ናቸው፡፡

እንደ አቶ ፍቃዱ ገለጻ፤ ኢፕድ የኢትዮጵያን የ82 ዓመት ታሪክ በጋዜጣና በፎቶ ሰንዶ የያዘ አንጋፋ ተቋም ነው፡፡ በተቋሙ የብዙ ተቋማት ታሪክ ይገኛል። ከዚህ አንፃር የተለያዩ ተቋማት የፎቶ ዓውደ ርዕይ ድርጅቱ እንዲያዘጋጅላቸው ይጠይቃሉ። በቱሪዝም ሳምንቱ የቀረበው የፎቶ ዓውደ ርዕይ የዚሁ አካል መሆኑን ገልጸዋል።

ኢፕድ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ ለኢቢሲ እና ለተለያዩ ተቋማት የፎቶ ዓውደ ርዕይ አዘጋጅቷል። አሁን ደግሞ በቅርቡ ለዕይታ የሚቀርብ የፎቶ ዓውደ ርዕይ እያዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል።

በዓውደ ርዕዩ ከ200 በላይ ፎቶ ግራፎች ለዕይታ የቀረቡ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር፣ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ አቶ ዣንጥራር ዓባይ እና የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) ዓውደ ርዕዩን መርቀው ከፍተዋል።

ዓውደ ርዕዩን ከጥቅምት 20 እስከ 22/2016 ዓ.ም ድረስ በመስቀል አደባባይ ሁሉም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በነፃ መጎብኘት እንደሚችል ታውቋል።

# ቱሪዝምን ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በተለይ ከተማዋ ያሏትን የቱሪስት መዳረሻዎች በማስተዋወቅና በማልማት ከቱሪዝም የሚገኘውን ፈርጀ ብዙ ተጠቃሚነት ማሳደግ የሚያስፈልግ መሆኑን ጠቁመዋል።

ቱሪዝም አካታችና ሁሉንም የሚያቅፍ ዘርፍ መሆኑን በመገንዘብ ቅንጅታዊ አሠራርን በመዘርጋት የሀገሪቱን ገቢ ማሣደግ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

የቱሪዝም ዘርፍ ብዙ ያልተሠራበት ኢንዱስትሪ መሆኑን አንስተው፤ ያለውን ተፈጥሮን በመጠበቅ፣ በማልማትና ለሰው ልጅ ተስማሚ በማድረግ ዘርፉን ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

የከተማዋን የአየር ንብረት መዛባት መታደግ የሚችል ልዩ ልዩ መዳረሻዎችንና መስህቦችን እያለማን ነው ያሉት አቶ ጃንጥራር፤ በዚህም በከተማዋ የነበረውን 2 ነጥብ 8 በመቶ የአረንጓዴ ሽፋን ወደ 15 በመቶ ማሳደግ መቻሉን ገልጸዋል።

በመርሐ ግብሩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አፈጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር በበኩላቸው የቱሪዝም ሳምንት በሀገሪቱ በተለያዩ ምክንያቶች የተቀዛቀዘውን የቱሪዝም ዘርፍ የሚያነቃቃ መሆኑን አመልክተዋል።

በቱሪዝም ሳምንት ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ የሚባለውን የቱሪዝም ዘርፍ ፅንሰ ሀሳብ ላይ ግንዛቤ መፍጠር እንደሚገባ ጠቁመው፤ በከተማዋ ብሎም በሀገሪቱ ያሉትን ዕምቅ የቱሪዝም አቅሞችን በማልማት ወደ ቱሪዝም መስህብነት መቀየር እንደሚገባም ተናግረዋል።

ከተማዋን ከቱሪስት መተላለፊያነት ወደ ቱሪስት መዳረሻነት ለመቀየር ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ገልጸው፤ የለሙትን የቱሪዝም መስህቦችን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጎብኚዎች በማስተዋወቅ ወደ ምንዛሪ ለመቀየር እንደሚገባም አስታውቀዋል።

ለዚህም የቱሪስት መስህቦችን በማልማት፣ የቆይታ ጊዜ በማራዘምና ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ፣ እንዲሁም የከተማዋ ነዋሪ እየተሠሩ ባሉ ሥራዎች በመሳተፍ ለትውልድ የሚተርፍ አሻራ እንዲያሳርፉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

በመርሐ ግብሩ የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሣው እንደገለጹት፤ ዘንድሮ የሚከበረው የቱሪዝም ቀን መሪ ቃል ከተማዋ ላይ በአረንጓዴ ልማት ዘርፍ ረገድ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ያሳያል ።

አዲስ አበባ ከተማን ውብ፣ ፅዱ እና አረንጓዴ በማድረግ ከተማዋን ብሎም የሀገሪቱን የቱሪዝም ፍሰት ለመጨመር ይሠራል ያሉት ኃላፊዋ፤ ለዚህም የከተማው ነዋሪ በከተማው የሚገኙ የቱሪዝም ሀብቶችን ጠንቅቆ በማወቅ የቱሪዝም አምባሳደር በመሆን አለበት ብለዋል።

በቀጣይም አረንጓዴ ልማት ላይ በስፋትና በትኩረት የሚሠራ ሲሆን ይህም ለቱሪዝም እድገቱ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል ። በተጨማሪም በኮንፈረንስ ቱሪዝምና በጤና ቱሪዝም ትኩረት እንደሚሠራ አመልክተዋል።

# ንግድና ግብይት

## የተጋረጡበትን ማነቆዎች መሻገር የተሳነው የስጋ ወጪ ንግድ

ፍሬሕይወት አወቀ



ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በእንስሳት ሀብቷ ዕምቅ አቅም ቢኖራትም በስጋ ወጪ ንግድ የሚፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት እንዳልቻለች ይነገራል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ከምክንያቶቹ መካከልም በእንስሳት አቅርቦትና ጥራት ላይ የሚታየው ክፍተትና የኮንትሮባንድ ንግድ በዋናነት የሚጠቀሱ የዘርፉ ማነቆዎች እንደሆኑ በተደጋጋሚ ይነሳል። ያም ሆኖ ግን ላለፉት በርካታ ዓመታት ኢትዮጵያ የስጋ ምርት ወደ ውጭ ገበያ ስትልክ ቆይታለች።

በሀገሪቱ ከሚገኙ 11 ስጋ አምራችና ላኪ የኤክስፖርት ቄራዎች መካከል ሁለቱ በውጭ ባለሀብቶች የሚመሩ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ በሙሉ ሀገር በቀል በሆኑ ባለሀብቶች ይመራሉ። ሀገሪቷ በእንስሳት ሀብት ያላትን ዕምቅ አቅም ተገንዝበው ወደ ዘርፉ እንደገቡ የሚገልጹት ባለሀብቶች በሀገሪቱ ያለውን የእንስሳት ሀብት አሟጦ ለመጠቀም ዘርፈ ብዙ ችግሮች እንዳሉና ይህን ማለፍ እንዳልተቻለ አስረድተዋል።

የስጋ ምርትን ወደ ውጭ ገበያ እየላኩ ከሚገኙ የውጭ ባለሀብቶች መካከል አላና ግሩፕ አንዱ ነው። አላና ግሩፕ በዓለም ላይ አሉ ከሚባሉ የሀላል ስጋ አምራችና ላኪ ድርጅቶች መካከል ተጠቃሽ እንደሆነ የአላና ግሩፕ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ከሊፋ ሁሴን ይናገራሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ ሀላል ስጋ በማምረት የሚታወቀው አላና ግሩፕ በሕንድ ባለሀብቶች የሚመራ ሲሆን፣ ዋና መቀመጫውን ሕንድ በማድረግ 72 ለሚደርሱ የዓለም ሀገራት ስጋና የስጋ ምርቶችን ይልካል። ለዚህም 17 የሚደርሱ ኤክስፖርት ቄራዎች አሉት።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት ኤክስፖርት ቄራዎች ያሉት ሲሆን፣ አንደኛው ሞጆ ላይ ሁለተኛው ደግሞ አዳሚ ቱሉ ዝዋይ ላይ የሚገኝና በአፍሪካ ትልቁ ቄራ ነው። ኤክስፖርት ቄራዎቹ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተገነቡና ሰፊ ገበያ መዳረሻ ያላቸው ቢሆኑም በአሁን ወቅት በአቅማቸው ልክ እያመረቱ አይደለም የሚሉት አቶ ከሊፋ፤ አዳሚ ቱሉ ላይ የሚገኘው ቄራ ብቻ በቀን ዘጠኝ ሺ በግና ፍየል እንዲሁም ሦስት ሺ ከብት አርዶና አቀነባብሮ የመላክ አቅም አለው። ይሁንና በሀገሪቱ ካለው የአቅርቦት እጥረት የተነሳ በቀን ከሁለት ሺ እንስሳ በላይ እያረደ አለመሆኑ ነው ያስረዱት።

ለዚህም ዋናው ችግር የእንስሳት አቅርቦትና ኮንትሮባንድ ንግድ መሆኑን ያነሱት አቶ ከሊፋ፤ ሀገሪቱ በእንስሳት ሀብት ትልቅ አቅም ያላት ቢሆንም ወደ ገበያ የሚመጣው እንስሳት ቁጥር ግን አነስተኛና ጥራቱን የጠበቀም አይደለም ይላሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የእንስሳት ዋጋ ተወዳዳሪ አለመሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም ለዘርፉ ዕድገት ትልቅ ማነቆ እንደሆነ አስረድተዋል። በአሁኑ ወቅትም በዋጋ ንረቱ ምክንያት እንደ ሀገር የበሬ ስጋ ሙሉ ለሙሉ ኤክስፖርት ማድረግ እንዳልተቻለ አመላክተዋል።

‹‹አብዛኛው ስጋ ላኪ ስጋን በኪሳራ እየላከ ነው›› የሚሉት አቶ ከሊፋ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የስጋ ወጪ ንግዱ ይበልጥ እየተቀዛቀዘ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ለዚህም መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት መስጠት እንዳለበት ነው የገለጹት። ዘርፉ የመንግሥትን ድጋፍ ካገኘና የተጋረጡበትን ችግሮች መሻገር ከቻለ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ያለው አበርክቶ ከፍተኛ እንደሆነ ነው ያስረዱት።

ሀገር በቀል ከሆኑ ኤክስፖርት ቄራዎች መካከል አንዱ የሆነው የአቢሲንያ ኤክስፖርት ቄራ መሥራችና ባለቤት አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ በበኩላቸው፤ ዘርፉን ከተቀላቀሉ ዘጠኝ ዓመታትን እንዳስቆጠሩ ገልጸው ወደ ውጭ ገበያ የሚልኩት የስጋ መጠን ከዓመት ዓመት እየቀነሰና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የመሆን ዕድላቸው እየቀነሰ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ሀገሪቷ በእንስሳት ሀብት ትልቅ አቅም ያላት ቢሆንም በአቅርቦትና ጥራት ላይ እንዲሁም የኮንትሮባንድ ንግዱ እጅግ ፈታኝ ነው። በተለይም በቁም እንስሳት እየተፈጸመ ያለው የኮንትሮባንድ ንግድ የዘርፉ ዋነኛ ማነቆ ነው። በዚሁ ምክንያት የሚከሰተውን የዋጋ ንረት መቆጣጠር አልተቻለም። የአቅርቦት እጥረትም ሌላው ችግር ሲሆን እንስሳቱን የሚያቀርበው አርብቶአደሩ ነው። አርብቶአደሩ ገንዘብ ሲፈልግ ብቻ የሚያመጣውን እንስሳት ጠብቆ የውጭ ገበያን መወዳደር አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ በዋነኛነት የስጋ ወጪ ንግዱን ለማሳደግና ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ከፍ ለማድረግ ለኤክስፖርት ገበያ ተብሎ ብቻ እንስሳትን ማርባት ያስፈልጋል። ለዚህም ከግል ባለሀብቱ በበለጠ የመንግሥትን ድጋፍና ክትትል ያስፈልጋል ብለዋል።

‹‹የቁም እንስሳት ኮንትሮባንድ ንግድ በተለይም ሀገሪቷ በአሁኑ ወቅት ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተያይዞ እጅግ የተጠናከረበት በመሆኑ የውጭ ንግዱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው›› የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ፤ ዘርፉ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት የሚያስፈልገው እንደሆነ አመላክተዋል። አስፈላጊውን ትኩረት ካገኘና የግብይት ሥርዓቱን ጤናማ ማድረግ ከተቻለ ዘርፉ አሁን ካለበት ደረጃ በእጥፍ ማደግና ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ማምጣት የሚያስችል ትልቅ አቅም እንዳለው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ስጋ አምራች ላኪዎች ማኅበር ዋና ጸሐፊ አቶ አበባው መኮንን በበኩላቸው በሀገሪቱ የስጋ ወጪ ንግድ ኢንዱስትሪ ረዘም ያሉ ዓመታትን ያስቆጠረና ከስድስት በማይበልጡ ቄራዎች መጀመሩን አስታውሰው፤ አሁን ያለው የስጋ ወጪ ንግድ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር እየወረደ መሆኑን ነው የገለጹት። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ የሚገኙ የኤክስፖርት ቄራዎች ዝቅተኛ አፈጻጸም እያስመዘገቡ እንደሆነ ተናግረዋል።

ይሁንና ሀገሪቱ ካላት እምቅ የእንስሳት ሀብት ጋር ሲነጻጸር አሁን ላይ ለውጭ ገበያ እየቀረበ ያለው መጠንና ዘርፉ እያስመዘገበ ያለው የውጭ ምንዛሪ ዝቅተኛ መሆኑን ይገልጻሉ። ምንም እንኳን መንግሥት ባደረገው ጥረት የቄራዎችን ቁጥር ማበራከትና የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ወደ ኢንቨስትመንቱ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታዎች የተፈጠሩ ቢሆንም የኤክስፖርት መጠኑን ግን ማሳደግ አልተቻለም የሚሉት አቶ አበባው፤ በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ከሚገኙ 11 ኤክስፖርት ቄራዎች የሚገኘው የኤክስፖርት ገቢ በሚፈለገው ልክ እንዳልሆነ ነው ያስረዱት።

በኢንቨስትመንት ልክ ኤክስፖርት ማድረግ እንዳልተቻለ የጠቀሱት አቶ አበባው፤ በ2014 በጀት ዓመት ከስጋ ወጪ ንግድ 120 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን አስታውሰው፤ በ2015 በጀት ዓመት 14ሺ575 ቶን ስጋ ተልኮ፤ 89 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር መገኘቱን ተናግረዋል። በ2016 በጀት ዓመት 25 ሺ 607 ቶን ስጋ በመላክ 135 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለማግኘት መታቀዱን ገልጸዋል።

ለስጋ ወጪ ንግዱ መውረድ አንደኛው የዋጋ ንረት እንደሆነ የጠቀሱት አቶ አበባው፤ ለዋጋ ንረቱ መባባስም ሀገሪቱ ያለችበት የሠላምና ጸጥታ ችግር አንዱ ሲሆን፤ ሌላው የኮንትሮባንድ ንግዱ መባባስ በዋነኛነት የሚጠቀስ እንደሆነ አመላክተው፣ በዚህም የስጋ ወጪ ንግዱ አፈጻጸም ከዓመት ዓመት ዝቅተኛ እየሆነ መምጣቱን ተናግረዋል።

ኤክስፖርት ቄራዎች ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ የሚጠይቁ በመሆናቸው ባለሀብቶቹ ትልቅ ሀብት ያወጡበት መሆኑን ያነሱት አቶ አበባው፤ በሀገሪቱ ያሉ ኤክስፖርት ቄራዎች ከጥራት አንጻር ተወዳዳሪና ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ቄራዎች እንደሆኑም ተናግረዋል። በዘርፉ የተሰማሩት ስጋ አምራችና ላኪዎችም ከአስር ዓመታት በላይ ያስቆጠሩ እንደመሆናቸው ጥሩ ልምድ ያላቸውና ዓለም አቀፍ ገበያው ውስጥ መግባት እንደቻሉ ተናግረዋል። የስጋ ኢንዱስትሪ በባህሪው ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ የሚፈልግ ከመሆኑ ባሻገር ኢንቨስትመንት ውስጥ ለመግባትም የተለያዩ መስፈርቶችን የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም ስጋ አምራችና ላኪዎች በሀገር ውስጥ ተቆጣጣሪዎች ተገምግመው እንዲሁም በተቀባይ ሀገር ዓለም አቀፍ የሆነውን ሂደት አልፈው ወደ ኤክስፖርት ሥራው የሚገቡ እንደሆነም አቶ አበባው አስረድተዋል።

ገበያው ዓለም አቀፍ እንደመሆኑ ስጋ አምራችና ላኪዎች እንደ ሀገር የተሻለና ጥራት ያለው ምርት ይዘው መቅረብ አለባቸው የሚሉት አቶ አበባው፤ ለዚህም ቀሪ የቤት ሥራዎችን መሥራት የግድ የሚል ነው ይላሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ በአሁኑ ወቅት በሀገር ውስጥ ያለው የስጋ መግዣ ዋጋ ዘርፉን በእጅጉ እየፈተነው ነው። በተለይም ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በሀገር ውስጥ ያለው የስጋ መግዣ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ በመሆኑ ዋጋውን መቆጣጠር አልተቻለም። ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ›› እንዲሉ ሆኖ የእንስሳት አቅርቦት እጥረቱም ከፍተኛ ነው። ኤክስፖርት ቄራዎቹም የደንበኞቻቸውን ፍላጎት ለማሟላት ሲሉ አላስፈላጊ ውድድር ውስጥ ይገባሉ። በእነዚህና መሰል ምክንያቶች በዓለም አቀፉ ገበያ ያለው የስጋ መሸጫ ዋጋ ከኬንያ፣ ከታንዛኒያና ከሱዳን ጋር ሲነጻጸር የኢትዮጵያ ከፍተኛ ነው። ይህም ኤክስፖርት ቄራዎቹ ተወዳዳሪና አትራፊ ሆነው መቀጠል አላስቻላቸውም።

የአቅርቦት እጥረት ዋነኛው የዘርፉ ማነቆ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ አበባው፤ እንደ ሀገር ያለው የእንስሳት ልማት ሥራው ኋላቀርና የግብይት ሥርዓቱም ጤናማ እንዳልሆነ ይናገራሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ላይ ኤክስፖርት ቄራዎች እንስሳቱን የሚያገኙት ከአርብቶ አደሩ ሲሆን፤ አርብቶ አደሩ እንስሳቱን ለኤክስፖርት ቄራ ብሎ የሚያረባ እንዳልሆነና ባህላዊ በሆነ መንገድ በቤቱ ያረባውን ወደ ገበያ ያወጣል። ከዚህም ባለፈ አርብቶ አደሩ ገንዘብ ሲፈልግ ብቻ እንስሳቱን ወደ ገበያ አውጥቶ ይሸጣል። ስለዚህ አርብቶ አደሩ ለኮንትሮባንድም ይሁን ለኤክስፖርት ቄራዎች የተሻለ ዋጋ ለሰጠው የሚሸጥበት መንገድ ነው ያለው። ይህም የገበያ ሥርዓቱን ፈታኝ አድርጎታል።

ለአቅርቦት እጥረቱም ሆነ ለገበያው ችግር መፍትሔ መሆን የሚችለው እንስሳቱን ለኤክስፖርት ቄራ ተብሎ ማርባት ሲቻል እንደሆነ ያመላከቱት አቶ አበባው፤ እንስሳትን ለኤክስፖርት ቄራ ለማቅረብ እስካሁን በመንግሥት በኩል የተደረገ ጥረት አለመኖሩን ገልጸዋል። ሆኖም ግን አንዳንድ ኤክስፖርት ቄራዎች ለራሳቸው ቄራ ግብዓት መሆን የሚችሉ እንስሳትን ለማርባት ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ባለሀብቱ ብቻውን ሊያሳካው እንደማይችል በመሆኑ ዳር ማድረስ አልተቻለም። ምክንያቱም ትልቅ ኢንቨስትመንት እንደመሆኑ የመንግሥትን ከፍተኛ ድጋፍና ክትትል ይፈልጋል። ለእንስሳት እርባታ ዘርፉ ሰፊ መሬት፣ የውሃ አቅርቦትና ሌሎች መሠረተ ልማቶችን የሚፈልግ ነው። ለዚህም የመንግሥትን ቁርጠኛ አመራር ይፈልጋል። ይሁንና እስካሁን የተደረጉ ሙከራዎችና ጥረቶች የሉም ብለዋል።

ነገር ግን መንግሥት ለዘርፉ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ለኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆን እንስሳት ማርባት የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ከቻለ ኢንዱስትሪውን ማሳደግ ይቻላል የሚሉት አቶ አበባው፤ ይህን አሠራር መከተል ካልተቻለ ከአርብቶአደሩ የሚገኝ እንስሳትን ብቻ ጠብቆ ኤክስፖርትን ማሳደግ የማይቻል እንደሆነ አመላክተው፤ ይህም የዘርፉ ማነቆ እንደሆነ በተጨባጭ መታየቱንም ያስረዳሉ።

በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች የመንግሥትን ድጋፍ ካገኙ ለእንስሳት እርባታ ሥራው ፈቃደኞች እንደሆኑ ጠቅሰው፤ ከኤክስፖርት ቄራ ውጪ የሚገኝ ማንኛውም ባለሀብትም እንዲሁ እንስሳትን ለኤክስፖርት ቄራ ብቻ አርብቶ ማቅረብ ከፈለገ በሩ ክፍት እንደሆነ ገልጸዋል። ለዚህም ከፍተኛ የሆነ የመንግሥትን ትኩረትና ድጋፍ ይፈልጋል ነው ያሉት።

የገበያ መዳረሻ ሀገራትን አስመልክቶ አቶ አበባው እንዳሉት፤ እስካሁን ባለው የተባበሩት ዐረብ ኢሚሬትስ፣ ዱባይ፣ ሳውዲዐረቢያና ሪያድ የመሳሰሉ ሀገራት 90 በመቶ ያህል የገበያ ድርሻ ያላቸው ሲሆን፤ ኩዌትና ኳታርም እንዲሁ ድርሻ አላቸው ብለዋል። ቻይናን ጨምሮ ሆንግኮንግና ቬትናም ደግሞ የዕርድ ተረፈ ምርት ገዢ ሀገራት ናቸው።

አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ለማስፋት በዋናነት ሁለት ነገሮች ያስፈልጋሉ የሚሉት አቶ አበባው፣ አንደኛ ምርቱን ማስተዋወቅና በዘርፉ ያለውን ምቹ ሁኔታ ለተቀባይ ሀገራት የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት አንዱ ነው። ሁለተኛው የምግብ ምርት እንደመሆኑ ከእንስሳት ጤና ጋር ተያይዞ ዓለም አቀፍ ደረጃውን መሠረት በማድረግ የሚቀመጥ መስፈርት ማሟላት ሲሆን፤ እስካሁን ተሟልቶ እየተላከ ያለውም መካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ብቻ ነው። በቅርቡ የቻይና ገበያን ተደራሽ ለማድረግ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ስለመኖራቸው ጠቅሰው፤ ይህም ተስፋ ሰጪ እንደሆነ አመላክተዋል። ሀገሪቱ አሁን ያለችበትን የእንስሳት ጤና አጠባበቅ አጠናክሮ መቀጠል ከተቻለ ወደ ገበያው የመግባት ዕድል አለ ብለዋል።

እንደ ሀገር በእንስሳት ሀብት ትልቅ አቅም መኖሩንና ይህን ሀብት አሟጦ በመጠቀም ሀገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ውጤት ማግኘት እንድትችል ቀሪ የቤት ሥራዎች ስለመኖራቸው ያነሱት አቶ አበባው፤ እስካሁን ባለው ሂደትም ከኢንቨስትመንት አንጻር ኢንዱስትሪው ላይ ትልቅ አቅም መፍጠር እንደተቻለ ገልጸዋል። በመሆኑም በሀገሪቱ የሚገኙ 11 የኤክስፖርት ቄራዎች በዓመት እስከ ሁለት መቶ ሺ ቶን ስጋ አምርተውና አቀነባብረው ለዓለም ገበያ የማቅረብ አቅም እንዳላቸው ተናግረዋል።

ይህም የስጋ ወጪ ንግዱ ከሌሎች የኤክስፖርት ዘርፎች ባልተናነስ መንገድ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ለሀገሪቱ ማምጣት እንደሚችል የሚያሳይ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አበባው፤ ዘርፉ ለሀገሪቱ ከሚያመጣው የውጭ ምንዛሪ ግኝት ባለፈም አርብቶ አደሩን ጨምሮ በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን በሙሉ ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚችል አስረድተዋል። አያይዘውም መንግሥት በዘርፉ ከተሰማሩ ባለሀብቶች ጋር ተቀራርቦና ተቀናጅቶ መሥራት የሚጠበቅበት እንደሆነ አብራርተዋል።

መንግሥት ለዘርፉ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ ሊከታተለው የሚገባው ዘርፍ እንደሆነ የገለጹት አቶ አበባው፤ በተለይም ከፖሊሲ አንጻር የመንግሥትን ውሳኔ በሚፈልጉ ጉዳዮች ተሳትፎውን ማጠናከር እንደሚገባ አመላክተው እነዚህንና መሰል ችግሮችን መፍታት ከተቻለ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ከፍ ማድረግ የሚቻልበት ሰፊ ዕድል መኖሩን ተናግረዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የሠለጠነ ዜጋ ወቃሽ ሳይሆን ነቃሽ ነው

**ዋስልኝ አየለ**

ብዙዎቻችን ወቃሾች ነን እንጂ ችግሩን ለመቅረፍ ራሳችን ጥረት አናደርግም። ለምሳሌ፤ ሕግ ባለመከበሩ መንግሥትን እና ሕግ የጣሱ አካላትን እንወቅሳለን። ‹‹መቼ ይሆን እዚች ሀገር ላይ ሕግ የሚከበረው?›› እንላለን፤ ዳሩ ግን የመፍትሔው አካል ለመሆን አንሠራም። በብልሹ አሠራሮች እናማርራለን፤ ዳሩ ግን ያንን ብልሹ አሠራር ለማስቀረት ጥረት አናደርግም፤ ይባስ ብሎ ተባባሪ የምንሆንበት አጋጣሚም አለ።

ይህን ያስታወሰኝ ከሰሞኑ የአንድ ምሁር ገጠመኝ በማኅበራዊ ገጻቸው ላይ አንብቤ ነው። ኢንጂነር ጌታሁን ሄራሞ ይባላሉ። በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ላይ እየተጋበዙ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ። በማኅበራዊ ገጻቸውም በፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን ይጽፋሉ። ባለፈው ሳምንት የጻፉትን ገጠመኝ ግን ለብዙዎቻችን ልምድ መሆን ስላለበት ወዲህ አመጣሁት። ገጠመኛቸውን ቃል በቃል ልውሰደውና የሚከተለው ነው።

‹‹...ከሥር ያስቀመጥኩት ፎቶ (በማኅበራዊ ገጻቸው ላይ ተቀምጧል) የሚያመለክተው ከአለርት ሆስፒታል ወደ አየር ጤና አደባባይ ለመድረስ ጥቂት ሜትሮች ሲቀሩ የትራፊክ ምልክት ተብሎ በመንገዱ አካፋይ የተተከለ ነው፤ መኪናውን አቁሞና ወርዶ ብቻ ነው ምንነቱን ማወቅ የሚቻለው።

እንግዲህ ትናንት ወደ 10:30 አካባቢ ይህ ምልክት በምልክትነት ተቆጥሮ ሦስት የመንገድ ትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎችና አንድ የሴት ትራፊክ ፖሊስ ወደ መጡበት አቅጣጫ U-Turn የሚመለሱትን መኪናዎች አስቁመው እንደ ጉድ እየቀጡ ነበር። ባለመኪኖቹም ያለአንዳች ማንገራገር በቴሌ ብር ቅጣቱን እየከፈሉ ይሄዳሉ። እኔም የመቀጣት (ቅጣት ከተባለ) ዕጣው ደርሶኝ ከሦስት የትራፊክ መንገድ ሠራተኞች አንዱ ሙግቴን ተከትሎ የቅጣት ወረቀቱን ፃፋብኝ። ከመንገድ ትራንስፖርት ሠራተኛው ጋር በነበረኝ ቆይታ የታዘብኳቸው አራት ነጥቦች፤

አንደኛ፤ ዋናው ምልክቱ ወደ ሌላ አቅጣጫ በዞረ እና ፈፅሞ በማይታይ ምልክት ለምን ትቀጣላችሁ? ስለው፣ ምልክቱ እንደማይታይ አምኖ እኔን ግን... እሱን ሂድና ትራፊክ ጽሕፈት ቤት አመልከት... በማለት ጋጠወጥ ምላሽ ሰጠኝ። እሱን ከእኔ ይልቅ አንተ ነህ መጠቆም ያለብህ በምልበት ደቂቃ እሱ የቅጣት ማዘዣውን በመፃፍ ‹‹ቢዚ›› ነበር።

ሁለተኛ፤ እኔን ቀድሞ የታጠፈ ሌላ መኪና ነበር፤ እኔን ያስቆመኝ እሱን ትቶ ነው። እንደዚህ ሚዛናዊ ባልሆነ መልኩ እየመረጣችሁ መቅጣቱንስ ሕጉ ይፈቅድላችኋል ወይ? በማለት ስጠይቀው ‹‹አምልጦ ነው የሄደው፤ ታርጋውን ይዘናል›› አለኝ። ሚዛናዊነታችሁን ማረጋገጥ ስላለብኝ የያዛችሁትን ታርጋ አሳዩኝ ስለው፤ ‹‹እንዲያውም አያገባህም›› የሚል ምላሽ ሰጠኝ። ታርጋውን ይዘናል ያለው ውሸቱን ነበር።

ሦስተኛ፤ በቅጣት ወረቀቱ ላይ ከሥር ቅጣቱን የፃፈው ሠራተኛ ስም እንዲፃፍ የሚጠይቅ ቦታ አለ። ቦታው ላይ የመንገድ ትራንስፖርት ሠራተኛው የራሱን ስም ብቻ ነበር የፃፈው። እኔም የአባትህንም ስም ጨምረህ ፃፍልኝ ብዬ ስጠይቀው ‹‹የእኔ ስም ብቻውን በቂ ስለሆነ የአባቴን ስም አልፅፍም›› ብሎ በቁጣ ተናገረኝ።

ጉዳዩን ለማመልከት ወደ ኮልፌ ቀራኒዮ የመንገድ ትራንስፖርት ጽሕፈት ቤት ስሄድ 11፡00 ሰዓት ሞልቶ ነበርና ቢሮው ዝግ ነበር። ዛሬ ሄጄ የመንገድ ትራንስፖርት ሠራተኞቹን ጋጠወጥነትና የማን አለብኝነት ባሕርያቸው ምንጩ ምን እንደሆነ የሚመለከታቸውን ኃላፊዎች ለመጠየቅ ወስኜአለሁ።...››

ኢንጂነር ጌታሁን ፎክረው አልቀሩም። ጉዳዩን ሄደው በማመልከታቸውና ቅሬታቸውን በግልጽ በመናገራቸው የዞረው እና የማይታይ የነበረው የትራፊክ ምልክት ተስተካክሏል። የኮልፌ ቀራኒዮ ትራፊክ ማኔጅመንት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች በትህትና ቅሬታቸውን እንዳደመጡና ጥፋቱን የሠራው ሠራተኛም ይቅርታ እንደጠየቃቸው ተናግረዋል።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ መባል አለበት። ኢንጂነር ጌታሁን ምሁር ናቸው። እንደምናየው እንደምንሰማው ደግሞ በሀገራችን ምሁራን ብዙም ታዋቂ አይደሉም። ሃሳባቸው እንጂ ፊታቸው እንደ አርቲስት በብዙዎች ዘንድ የሚታወቅ አይደለም። ከኢንጂነር ጌታሁን ገጠመኝ ሥር ከተሰጡ አስተያየቶች ውስጥ አንተ ታዋቂ ስለሆንክ ነው ያስተናገዱህ የሚል ይዘት ያላቸው ነበሩ። እርሳቸውም ለእነዚህ አስተያየቶች በሰጡት መልስ ‹‹... ከይቅርታ ጋር እኔን እናንተ በምትሉት መልኩ ያወቀኝ የለም፤ የሚያውቁኝ መስሎኝ ዓይኔን ቁልጭ ቁልጭ ባደርግም ከዕውቅና ጋር በተገናኘ ከቁብ የቆጠረኝ አልነበረም (የፌስቡክ የሳቅ ምልክት)...››

ይህን የኢንጂነር ጌታሁን ሄራሞን ገጠመኝ ያመጣሁት ከኃላፊነታቸው ሁላችንም እንድንማር ነው። ብዙዎቻችን እናማርራለን እንጂ በዜጋዊ ኃላፊነት ችግሩን ለመቅረፍ አንሠራም። አንድ የስንፍና መሸፈኛ ዘዴ አለን። ይሄውም ‹‹እኔ ተናግሬ ለውጥ ላላመጣ...›› የሚል ነው። ሁሉም ሰው እንደዚህ ካለ ለውጥ አይመጣም። አብዛኛው ሰው ‹‹እኔ ተናግሬ ለውጥ ላላመጣ...›› የሚለው ተናግሮ ሳይሞክረው ነው። እርግጥ ነው ቀልጣፋ እና ፈጣን ምላሽ ይገኛል ማለቴ አይደለም፤ ዳሩ ግን በኃላፊነትና በጨዋነት ያስተዋልነውን ብልሹ አሠራር ለሚመለከተው አካል ብናሳውቅ ችግሩ ይቀንሳል። ምናልባት በድንፋታ እና በቁጣ ከተናገርን ግን ችግሩ ይባባሳል እንጂ አይቀረፍም።


ከዚህ በፊት አንድ ጓደኛዬ ከፖሊስ ጋር ተጣልቶ የነበረውን ገጠመኝ አስነብቤያችሁ ነበር። ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሊያመለክት ሲሄድ ‹‹ኧረ ተጨማሪ በጥፊ እንዳይሉህ›› እየተባለ ተቀልዶበት ነበር። ፖሊስ ጣቢያ በትህትና አስተናግደው ከተጣላው ፖሊስ ጋር ይቅርታ አባብለዋቸው ነበር ጉዳዩ ያለቀው።

አንዳንድ ጊዜ በስሚ ስሚ ብቻ ‹‹አያስተናግዱንም›› በሚል እንሳነፋለን። ችግር የፈጠረውን አካል ወይም ሕግና ደንብ የተላለፈውን አካል ከመጠየቅ ይልቅ ከቀበሌ እስከ ፌዴራል ያለውን የመንግሥት አካል መሳደብ ይቀለናል። ተከታትለን መጠየቅ ባህል እስካላደረግን ድረስ ሕግና ደንብ የሚጥሱ ሠራተኞች ይኖራሉ። የመጠየቅ ልማድ ከሌለን ማንም አይጠይቀኝም የሚል የልብ ልብ ነው የሚሰማቸው። እንዲህ እንደነ ኢንጂነር ጌታሁን ሄራሞ ዓይነት ጠያቂ የሰለጠነ ዜጋ ቢኖር ግን ሕዝብ ሊያገለግሉ ኃላፊነት የወሰዱ ሠራተኞች በሰው አይቀልዱም ነበር። አብዛኞቹ ከሕግና ደንብ ውጪ ሰዎችን ያለአግባብ የሚቀጡት ተጠያቂነት እንደማያጋጥማቸው እርግጠኛ ስለሚሆኑ ነው።

እንደ ዜጋ ሕግና ደንቦችን ማስተካከል የሁላችንም ግዴታ ነው። አንድን ኃላፊ የሚጠይቀው ሌላ የበላይ አካል ብቻ ነው ብለን ዝም ካልን ችግሩ አይቀረፍም፤ ምክንያቱም ያ ኃላፊ ከበላይ ኃላፊዎቹ ይልቅ ለባለጉዳዮች ይቀርባል። የሚያጠፋውን ጥፋት የሚያውቀው ባለጉዳይ እንጂ የበላይ አለቃው አይደለም፤ የበላይ አለቃው ሲመጣማ ትሁት፣ ታታሪና ተቆርቋሪ ነው የሚሆነው።

ብልሹ አሠራሮቻችን ተቀርፈው፣ ሕግና ደንብ ተከብሮ፣ የሠለጠነ አሠራር እንዲኖር ወቃሽ ብቻ ሳይሆን ነቃሽም እንሁን!

# ዓለም አቀፍ



በ2040 ከባድ አደጋዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ በእጥፍ ይጨምራሉ ተብሎ ይጠበቃል

## ተመድ ለሕይወት አስጊ የሆኑ ስድስት ስር ነቀል ለውጦችን አስጠነቀቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባወጣው ሪፖርት የሰውን ልጅ ሕይወት ሊለውጡ ስለሚችሉ በማኅበራዊ እና በአካባቢያዊ ሥርዓቶች ላይ የሚታዩ ስድስት ስር ነቀል ለውጦችን አስጠንቅቋል።

«የተያያዙ የአደጋ ስጋቶች 2023» በሚል ርዕስ የቀረበው ሪፖርት ሰዎችን እና ምድርን ስጋት ላይ ለሚጥሉ ስድስት አደጋዎች መፍትሄ አለመስጠት ወደፊት አደጋው እንደሚያድግ አጽንዖት ሰጥቷል።

ሪፖርቱ በማኅበራዊ ሥነ-ምህዳር ሥርዓት ውስጥ አደጋዎችን መቀነስ እና የሚጠበቀውን ተግባር መፈጸም በማይችልበት ቅጽበት ላይ መገኘትን መነሻ የስጋት ነጥብ አድርጓል።

የስጋት ነጥቦቹ ከግለሰብ የአየር ንብረት፣ ሥነ-ምህዳር፣ ከማኅበረሰብ ወይም ቴክኖሎጂ እይታ አልፈው እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው። በዙሪያችን ያሉ ሥርዓቶች እንደ ሥነ-ምህዳር፣ ምግብ እና የውሃ ሥርዓት ከሰዎች፣ ከሰው እንቅስቃሴ እና ኑሮ ጋር በቅርበት የተሳሰሩ ናቸው።

ሥርዓቱ እየቀነሰ ሲሄድ አለመረጋጋት ቀስ በቀስ ያድጋል። እ.አ.አ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ከአየር ንብረት ጋር በተያያዙ አደጋዎች የሚደርሰው ጉዳት በሰባት እጥፍ ጨምሯል። በ2022 ብቻ 313 ቢሊዮን ዶላር የዓለም ኢኮኖሚ ኪሳራ ደርሶበታል።

በ2040 ከባድ አደጋዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ በእጥፍ ይጨምራሉ ተብሎም ይጠበቃል።

በተጨማሪም አደጋ የሚደርስባቸው አካባቢዎች በቁጥርም በስፋትም ያድጋሉ ተብሏል። እንደ ሰደድ እሳት እና አውሎ ንፋስ ያሉ አደጋዎች ወደ አዲስ አካባቢዎች ስለሚሸጋገሩ አደጋ ላይ ያሉ አካባቢዎች ቁጥር እና መጠን ሊሰፋ ይችላል ተብሎ ይጠበቃል።

እነዚህ ለውጦች በኢንሹራንስ ዘርፉ ላይ ተጽዕኖ እያሳደሩ ሲሆን፤ የኢንሹራንስ አረቦን ከ2015 ጀምሮ በ57 በመቶ አድጓል ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

## ፑቲን በሀገራቸው ስተፈጠረው ፀረ-አይሁድ እንቅስቃሴ ምዕራባውያንን ተጠያቂ አደረጉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እሁድ ዕለት ከእስራኤል ቴልአቪቭ የተነሳው አውሮፕላን በሩሲያ አየር ማረፊያ በሚደርስበት ወቅት ጸረ- ሴማዊ ተቃውሞዎች መነሳታቸውን ተከትሎ ሩሲያ በዩክሬን እና በምዕራባውያን የተቀነባበረ ነው ስትል ወቀሰች።

አሜሪካ በምላሹ «የማይረባ» በማለት አጣጥላዋለች። የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በቴሌቪዥን በተካሄደ ስብሰባ ላይ እንደገለጹት፤ ክስተቱ «ሁከትን» ለማስፋፋት የተደረገ ሙከራ ነው። ከእስራኤል መዲና ቴል አቪቭ የተነሳ አውሮፕላን ማካችካላ ከመድረሱ በፊት በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አየር ማረፊያውን ወርረዋል። ብዙዎች የፍልስጥኤም ሰንደቅ ዓላማ ከማውለብለብ ባለፈ ጸረ ሴማዊ መፈክሮችን አሰምተዋል።

ዳግስታን በምትባለው የሩስያ ግዛት የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ነዋሪዎች ሙስሊሞች ናቸው። አጋጣሚው በጋዛ የተነሳው ግጭት የወለደው ንዴት የቀሰቀሰው ነው ተብሏል።

የጸጥታ ኃይሎች ሁኔታውን በቁጥጥር ስር አውለዋል። ከ60 በላይ ሰዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የአካባቢው ባለሥልጣናት ገልጸዋል። ፑቲን በሩሲያ የፀጥታ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ«የማካችካላው ክስተት ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም ዩክሬን ብቻ ሳትሆን የምዕራባውያን የስለላ እጅ ያለበት ነው» ብለዋል። «ሕይወት የሚቀጥፈውን ትርምስ ማን እያደራጀ ነው? ማንስ ይጠቀማል? በእኔ እምነት ጉዳዩ ግልጽ ነው።» «በዓለም አለመረጋጋት ዋነኛ ተጠቃሚ የሆኑት የአሜሪካ መሪዎች እና ተላላኪዎቻቸው ናቸው» ብለዋል።

የክሬምሊን ቃል አቀባይ ዲሚትሪ ፔስኮቭ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት «በጋዛ ሰርጥ ውስጥ እየተፈጸመ ያለውን አሰቃቂ ድርጊት የሚያሳዩ የቴሌቪዥን ምስሎች ምክንያት በማድረግ ጠላቶች አጋጣሚውን ተጠቅመው ለማነሳሳት በጣም ቀልሏቸዋል።»

የዳግስታን ገዥ ሰርጌይ ሜሊኮቭ በበኩላቸው ሁከቱ የተቀሰቀሰው «በዩክሬን ግዛት ባሉ ከዳተኞች» ሞርኒንግ ዳግስታን የተባለውን የቴሌግራም ቻናል በመጠቀም መሆኑን ገልጸዋል። ሞርኒንግ ዳግስታን እስላማዊ ቻናል ሲሆን ሩሲያን ክልሉን መቆጣጠሯን የሚቃወም ነው። በ2016 ከድቶ ወደ ዩክሬን በመግባት ዜግነት ካገኘው ከቀድሞው የሩሲያ የፓርላማ አባል ኢሊያ ፖኖማሬቭ ጋር ግንኙነት አለው።

እሑድ ዕለት ቻናሉ ከቴል አቪቭ ወደ ማካችካላ የተደረገውን በረራ ዝርዝር መረጃ አውጥቶ ተከታዮቹ «ጎብኚዎቹን እንዲያገኙ» መልዕክት አስተላልፏል።

የሜሊኮቭን አስተያየት ተከትሎ ቻናሉ ከፖኖማሬቭም ሆነ ከዩክሬን ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው መግለጫ አውጥቷል። ፖኖማሬቭ ባለፈው ዓመት ቻናሉን መደገፍ እንዳቆመ ተናግሯል። ምንም እንኳን በቅርብ ወራት የሰጣቸው መግለጫዎች ይህንን የሚቃረኑ ቢሆኑም። የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዜለንስኪ የአየር ማረፊያውን ሁከት አውግዘዋል። የአሜሪካ ብሔራዊ የጸጥታ ምክር ቤት ቃል አቀባይ ጆን ኪርቢ ስለ ሩሲያ ክስ ለቀረበላቸው ጥያቄ «የሩሲያ የምናቃቸው ትርክቶች ናቸው» ሲሉ መልሰዋል።

«በሀገራችሁ መጥፎ ነገር ሲከሰት ሌላን ወገን ትወቅሳላችሁ» ብለዋል። «ምዕራባውያን ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም። በቀላሉ ይህ ጥላቻ፣ ጭፍን ጥላቻ እና ማስፈራራት ነው።» ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የአውሮፕላን ማረፊያው ሁኔታ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነበሩ ፖጎም ተብለው የሚጠሩት የእስራኤላውያን ጭፍጨፋ ምስሎች ጋር መነጻጸሩ «ትክክለኛ» ነው ብለዋል። በማህበራዊ ድረ ገጾች ላይ በስፋት የተሰራጨው ተንቀሳቃሽ ምስል በርካታ ሰዎች ወደ አውሮፕላን ማረፊያው በኃይል ገብተው በሮች ከፍተው ወደ አውሮፕላን መንደርደሪያው ሲያቀኑ ያሳያል።

የተወሰኑት ደግሞ የእስራኤልን ፓስፖርት የያዙ ሰዎችን ለመፈለግ በሚመስል መልኩ መኪናዎችን ሲያቆሙ እና የተሳፋሪዎቹን ሰነዶች ሲጠይቁ ታይተዋል። የሩሲያ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የፖሊስ አባላትን ጨምሮ 20 ሰዎች ጉዳት እንደደረሰባቸው እና ሁለቱ በአስጊ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ ገልጿል።

የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ ጽሕፈት ቤት ባወጣው መግለጫ የእስራኤል መንግሥት «በየትኛውም ቦታ የሚገኙ የእስራኤል ዜጎችን እና አይሁዶችን ለመጉዳት የሚደረጉ ሙከራዎችን እንደ ጸብ አጫሪነት ይመለከታል» ብሏል። «የሩሲያ ባለሥልጣናት የሁሉም የእስራኤል ዜጎች እና አይሁዶች ደህንነታቸው እንዲጠብቅ እና ሁከት ፈጣሪዎች ላይ ጠንካራ እርምጃ እንዲወስዱ እስራኤል ትጠይቃለች» ሲል አክሏል ሲል የዘገበው ቢቢሲ አማርኛ ነው።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# «ከታላቁ ትርክት» በፊት…!?

በአአዩ የተዘጋጀ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡-” ተረከ ስለአለፈ ነገር ዘርዝሮ ተናገረ ፣ አወራ፣ አወጋ፣ አተተ ማለት ነው ይለናል።”ትርክት ደግሞ ስለአለፈ ነገር ዘርዝሮ የመናገርና የማውራት ሒደት ነው ። መንግሥታት ፣ ገዢዎችና የፖለቲካ ቡድኖች ቅቡልነትን ለማግኘትና ከተነሱበት ዓላማ አንጻር የዜጎችን ወይም የተከታዮቻቸውን እምነት፣ አመለካከትና እይታ ለመቃኘት ታሪኮችን ፣ ማስረጃዎችንና ገለጻዎችን አደራጅቶ ገዥ ሃሳብ አንጥሮ የመለየትና የማኸዘብ ስልት ነው ።

በእርግጥ ትርክት የጋራ ማንነትን ለማነጽ ያግዛል። በተለያዩ ማኅበረሰቦች ዘንድ አንድነትን ለመፍጠርና የጋራ ተግባር ለመትለም፤ የጋራ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ አላባውያንን በመጠቀም ብሔራዊ ማንነት ለመፍጠር ያስችላል። ከዚህ ባሻገር ትርክት ብሔራዊ እሴቶችንና ሕልሞችን ለመቅረጽ፤ ማኅበራዊ ስምምነት ለመፍጠር፤ ታሪካዊ ትውስታ ለመጫር፤ ሕዝብን ለአንድ ዓላማ ለማነሳሳት ንቅናቄ ለመፍጠርና ዓለምአቀፍ ገጽታ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር የማይተካ ሚና አለው።

በርግጥ ትርክት አዎንታዊና አሉታዊ ሊሆን ይችላል። ሀገርን ለመገንባት የሚውል አዎንታዊ ትርክት እንዳለ ሁሉ ሀገርን ለማፍረስ የሚውል አሉታዊ ትርክት እንዳለ በዘርፉ የተጻፉ ድርሳናት ያትታሉ። አዎንታዊ ወይም አካታች ትርክት አካታችነትን፣ ብዝኀነትንና ማኅበራዊ ውህደት ይሰብካል። አሉታዊ ትርክት በዜጎች መካከል ልዩነትን፣ ጥላቻን፣ አለመተማመንና መጠራጠርን የሚኀነቁል ከመሆኑ ባሻገር ሀገርን እስከማፍረስ ሊደርስ ይችላል። የሀገራችንን መልክና ሰማይ የሞላው ይህ አሉታዊ ትርክት ነው። ይህ አደገኛ ትርክት ሥራ ላይ እያለ አዲስ “ታላቅ ትርክት” ማንበር ያዳግታል። ለመሆኑ የዚህ ትርክት መነሻ ከወዴት ነው።

ለዚህ ይረዳ ዘንድ በከፊል አቅጣጫውን የሳተውና የጥራት እጥረት ያኮሰመነው እንዲሁም የአገዛዙ ነጸብራቅ የነበረው ሥርዓተ ትምህርትም መለስ ብሎ የመፈተሹ ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ከዚህ ጎን ለጎን ብሔራዊ እርቅና እውነትን የማፈላለግ እና በሀሰተኛ ትርክት የሴራ ደማሚት የፈረሱ የሕዝብ ለሕዝብ መገናኛ ድልድዮች መልሰው መጠገን አለባቸው

በተማሪዎች የ1960ዎች እንቅስቃሴ ከእነ ግርማቸው ለማ፣ መለስ ተክሌ (የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ስሙን የወረሱት )፣ ሰለሞን ዋዳ፣ ጥላሁን ግዛው ይልቅ ዛሬ ድረስ በበጎም፣ በክፉም ስሙ ከፍ ብሎ የሚወሳው የደሴው ዋለልኝ መኮንን ነው። ከእነ ሌኒን ማንፌስቶ እንዳለ ገልብጦ / ኮርጆ / ማታገያውን ከመደብ ጭቆና ወደ ጠባቡ የብሔር ጭቆና በማውረዱ ተደጋግሞ ቢወቀስም፤ አንዳንዶቹ ዋለልኝ የተማሪዎች ማህበር መሪዎች ያሳለፉትን ውሳኔ አነበበ፣ ጻፈ እንጂ የብሔር ጥያቄን ቀድሞም ሆነ ለብቻው አላነሳውም በማለት ጥያቄው የተማሪዎች እንቅስቃሴ የወለደው ስለሆነ ከዋለልኝ ጫንቃ ውረዱ የሚሉ ወገኖች አሉ።

ያም ሆነ ይህ በፈጠራ ትርክትና በግልብ ትንተና መታገያና ማታገያ ሆኖ የመጣው የብሔር ጥያቄ ሀገራችን ዛሬ ድረስ ለምትገኝበት ምስቅልቅል እና አጣብቂኝ መግፍኤ ከመሆኑ ባሻገር፤ ሀገር፣ ሕዝብ ብዙ ዋጋ አስከፍሏል። ከዚያን ጊዜ አንስቶ ልሒቃኑን በሁለት ጎራ ከፍሎ እያጨቃጨቀ ይገኛል። በሀገራችን ተንሰራፍቶ የነበረው ጭቆና የመደብ ነው አይደለም የብሔር ጭቆና ነው በሚሉ ሁለት የማይታረቁ ቅራኔዎች ተጠምዷል።

የብሔር ጭቆና በተጠየቃዊነት በምክንያታዊነት የሚተነተን ሳይሆን በማንነት በስሜት የሚቀነቀን የሚራገብ መሆኑ ልዩነቱን የማጥበብ ሂደቱን አዳጋች አድርጎታል። እዚህ ላይ በብሔርተኞች እና ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነትን በሚያራምዱ ወገኖች መካከል ያለውን ልዩነት በአብነት ማንሳት ይቻላል። ሆኖም የተማሪዎች እንቅስቃሴ ለትህነግ፣ ለኦነግና ለሌሎች የብሔር ድርጅቶች መፈጠር እርሾ ሆኖ ማገልገሉ አይካድም። ጉዳዩን በአግባቡ ለመረዳት በሰከነ መንፈስ ነገሮችን ማየት የሚጠይቅ ነው።

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴና ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ደጋግመው ባቀረቡት ምክረ ሃሳብ መሠረት ታሪካችንን መፈተሽ እንደገና መበየን ይጠይቃል። ይህን ስል እንደ በጀት ታሪካችን በቀመር ይደልደል ማለቴ ሳይሆን፤ ፍርጥርጥ፣ ግልጥልጥ ይበል፤ ሲለፈፍ በኖረው ትርክት ላይ በግልጥ ተነጋግረን እልባት እንስጠው ማለቴ ነው።

ወደ አገዛዝ ለመምጣት ሆነ በአገዛዝ ላይ ለመቆየት፤ ላለፉት 50 አመታት ልዩነቶችን የሚያሰፉ ጥላቻን መሠረት ያደረጉ ሥራዎች መዋቅራዊና ተቋማዊ ቅርጽ ይዘው በስፋት ተሠርተዋል፤ በዚህም ታሪክ ተበርዟል ፤ ሀሰተኛ ትርክት ተፈጥረሯል። ይህ አልበቃ ተብሎም ሀሰተኛ ትርክቶች ለገበያ ቀርበው እንዲሸጡ ተደርገዋል።

ይህንን ያልተገባ ትርክት ይዞ ብልጽግናናን በምልዓት ማረጋገጥ አይቻልም። ከፍ ሲልም ከ50 አመታት በኋላ ሒሳብ ስንተሳሰብ ከአተረፍነው ይልቅ የከሰርነው የትየለሌ ነውና። ከልዩነት ይልቅ አንድነትና ኢትዮጵያዊነት ላይ ተጠናክሮ ሊሠራ ፤ፖለቲካችንም በማንነት ሳይሆን በሃሳብ ሊኀለብት ሊታነፅ ይገባዋል። ለዚህ ደግሞ አዲስ ትርክት መቅረጽ ይጠይቃል።

ለዚህ ይረዳ ዘንድ በከፊል አቅጣጫውን የሳተውና የጥራት እጥረት ያኮሰመነው እንዲሁም የአገዛዙ ነጸብራቅ የነበረው ሥርዓተ ትምህርትም መለስ ብሎ የመፈተሹ ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ከዚህ ጎን ለጎን ብሔራዊ እርቅና እውነትን የማፈላለግ እና በሀሰተኛ ትርክት የሴራ ደማሚት የፈረሱ የሕዝብ ለሕዝብ መገናኛ ድልድዮች መልሰው መጠገን አለባቸው ።

ግማሽ ክፍለ ዘመን የተሻገረው ከብጥብጥና እርስ በእርስ በጥርጣሬና በጥላቻ ከመተያየት በቀር ብዙ ያላተረፈልን የፈጠራና የሀሰት ትርክት ልፋፌ ነቢብ እስከ ገቢር ያለው ምዕራፍ እልባት ሊያገኝ ይገባል።

የፈጠራ ትርክት ልፋፌ ነቢብ ከተቀዳበት ታሪካችን ብንነሳ ሁላችንም ባለዕዳ ነን። ሁላችንም ባለዕዳ ከሆን ደግሞ የየራሳችንን የፈጠራ ትርክት መቅረጽ እንችላለን። ችሎታችን ግን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ነው የሚሆነው። ማናችንም አናተርፍም። የዜሮ ድምር ፖለቲካ እንዲሉ ።

በአጭርና በጅምር ቀሩ እንጂ ታሪካችንንም እና አሁን “ሥራ ላይ ያለውን” ትርክት ለመፈተሽ እዚህም እዚያም ያልተቀናጁ ጥረቶች ተሞክረዋል። የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ በኢትዮጵያ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማሰባሰብ በኢትዮጵያ የታሪክ ትርክት ላይ ያተኮረ የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ እንደነበር ይታወሳል። እስካሁን ባለው የኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ያሉ አተያዮች ላይ ትኩረቱን ባደረገው የውይይት መድረክ፣ ኢዜማ ፣ አብን፣አነግ፣ አፌኮ፣ የሲዳማ ሕዝብ እና ሌሎችም የፖለቲካ ፓርቲዎች የመንግሥት ተቋማት፣ የሲቪክ ማኅበራት እንዲሁም ምሁራን ተሳትፈዋል።

በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች የሚንቀሳቀሱ ከ175 በላይ ሀገር በቀል የሲቪክ ማኅበራትን አቅፎ የያዘው ነው “የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ”። በመድረኩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር ፣ የታሪክ መጽሐፍ ሀያሲ እና «የድንቁርና ጌቶች» የተሰኘው መጽሐፍ ጸሐፊ በሆኑት በአቶ ብርሃኑ ደቦጭ አማካኝነት አከራካሪ ነው በተባለው በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የተጻፉ አተያዮችን በተለያየ ክፍል በማስቀመጥ በዝርዝር ቀርበዋል።

የሀገር ታሪክ፣ የመንግሥት ታሪክ፣ የብሔር ታሪክ የጎሳ/ዘር ታሪክ ሁሉም የራሱ ታሪክ ይኖረዋል ያሉት አቶ ብርሃኑ፤ ብሔራዊ ታሪክ ማለት እነኚህ ሁሉ በጋራ የሚቀመጡበት መሆኑን አስረድተዋል። እንዲህ ዓይነቱ ሥራ ብዙ ነገር እንደሚፈልግ፤ በተጨማሪም ጊዜ ፣ እውቀት፣ ልምምድ፣ ንግግር እና የሃሳብ ልውውጥም ይፈልጋል ብለዋል። ለዚህ ይመስላል ምን እየሠራ እንደሆነ መረጃ ባይኖረኝም ቀደም ባለው ጊዜ የታሪክ ምሁራን ያሰባሰበ ምክር ቤት እስከመመስረት የተደረሰው ።

**ሻሎም ! አሜን ።**

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# ከኦሎንኮሚ እስከ ነጩ ቤተመንግሥት

## ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኢጀታ

ክብረአብ በላቸው

የምሁር ዕውቀት የሰዎችን ኑሮና አኗኗር ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሻሻል የራሱን አስተዋፅዖ ማበርከት እንዳለበት ብዙዎች ይስማማሉ። በእያንዳንዱ የዕውቀት ዘርፍ የሚደረግ ጥናትና ምርምር የሰዎችን ሕይወት በማሻሻል ላይ ማዕከል ያደረገ መሆን እንዳለበትም እንዲሁ፤ ስለዚህ፣ አንድ ሰው በትክክል “ምሁር” ለመባል ብቁ የሚሆነው ዕውቀቱን ከራሱ አልፎ በሌሎች ሕይወት ላይ ለውጥና መሻሻል ለማምጣት የሚጠቀምበት ከሆነ ነው። ምሁርነትም ከዚህ አንፃር ታይቶና ተመዝኖ የሚሰጥ ክብር እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ።

ምሁር ለሚለው ቃል አቻ እንግሊዘኛ ትርጉሙ ኢንተለክቹዋል የሚለው ፍቺ ነው። የአማርኛ ቋንቋ ደግሞ ምሁር የሚለውን ቃል ከፍተኛ የሆነ የማሰብና የመመራመር ችሎታ ያለው ብሎ ይተነትነዋል ወይም ትርጉም ይሰጠዋል። በትምህርት የሚገኘው ዕውቀት በተግባር ለውጥና መሻሻል ካላመጣ ትምህርት መማሩና ማስተማሩ በራሱ ትርጉም የለውም ይላሉ ብዙዎች። የአንድ ሰው በትምህርት የተገኘ ዕውቀት ፋይዳ የሚኖረው በራስና በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ሲያስችል እንደሆነ በመግለፅ።

ምሁርን በተመለከተ በርካታ ሰዎች ጽፈዋል፤ ብዙዎቹ እንደሚናገሩት፤ ሁል ጊዜ ትልቁ የመከራከሪያ ነጥብ ብያኔውን በተመለከተ በግልፅ ማስቀመጥ አለመቻል ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አረዳድ ምሁር ማለት በአንድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ አልፎ ዲግሪ የያዘ ሰው ማለት ነው።

ምሁር ምን ማለት እንደሆነ ግን በምሳሌ በቀላሉ እንረዳለን። ሻማ ብንወስድና ሻማ በካርቶን ውስጥ እንዳለ በቤት ውስጥ ቢቀመጥ እንደማንኛውም በቤት ውስጥ እንዳለ ዕቃ ነው። የበራ ሻማ ግን ክስተት ነው። ሻማውን ከብርሃኑ ለይተህ አታየውም። የበራው ሻማ ለራሱ ሲል አይበራም ለሁላችን እንጂ፤ ምሁር ማለት የበራ ሻማ ማለት ነው። የተማረ ማለት ደግሞ ያልበራ ሻማ ማለት ነው፤ የመብራት አቅም አለው ነገር ግን አልበራም።

ስለዚህ ምሁር ማለት በልምድ፣ በትምህርትና በልዩ ልዩ መንገድ ያገኛቸውን ማስተዋሎችና ዕውቀት በሐሳብ መልክ ለኅብረተሰቡ የሚያቀርብ ሰው ነው። ለዚህ ቃል ብቁ ሆነው የተገኙ ጥቂት የሚባል ቁጥር የሌላቸው በዓለም መድረክ ላይ አዳዲስና ተጽዕኖ ፈጣሪ ግኝቶችንና ፈጠራዎችን ይዞ ብቅ በማለት የበርካቶችን አንገብጋቢ ችግር የፈቱና ብዙዎችን በስራዎቻቸው ያስገረሙ በርካታ ኢትዮጵያውያን አሉ። ከእነዚህም ልሂቃን መካከል የእርሻ ልሂቅና ተመራማሪ የሆኑት ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ እጃታ አንዱ ናቸው።

ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ እጀታ ከአዲስ አበባ በስተ ምዕራብ አቅጣጫ ስልሳ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቀት በሆለታ እና ጊንጪ ከተሞች መሃል ላይ በምትገኘው (ኦሎንኮሚ) በምትባል መንደር በ1942 ዓ.ም ተወለዱ። በወቅቱ በትምህርታቸው የላቀ ውጤት በማምጣት የሚታወቁት ፕሮፌሰር ገቢሳ እስከ 7ኛ ክፍል የተማሩት እዛው ኦሎንኮሚ ሲሆን የዘመናዊ ትምህርት ባካባቢው ባለመኖሩ ቤት ተከራይተው በክፍያ ከሚያስተምር ትምህርት ቤት ነበር የተማሩት:: ቤተሰባቸው በመለያየታቸው ምክንያት ሙሉ በሙሉ ልጃቸውን የማሳደጉ ኃላፊነት የወደቀባቸው እናታቸው ወ/ሮ ሙሉ አያነው ምንም እንኳን ኑሯቸው ከእጅ ወደአፍ ቢሆንም የልጃቸው የትምህርት ጉጉት እና ከእኩዮቹም እንዳይለይባቸው በማሰብ ጠላ እየሸጡ ያስተምሯቸው ነበር::

ፕሮፌሰር ገቢሳ የ8ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ደግሞ ከኦሎንኮሚ 20 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ በምትገኘው አዲስ ዓለም ከተማ ዘመድ ጋር በመቀመጥ ቀለባቸውን በየሳምንቱ እየተመላለሱ በመውሰድ አጠናቀቁ:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በወቅቱ ከኦክላሆማ ዩኒቨርሲቲ ጋር በትብብር በተከፈተው የጅማ የእርሻ የቴክኒክ ትምህርት ቤት ገብተው በከፍተኛ ማዕረግ በማጠናቀቅ የሐረማያ ዩኒቨርሲቲን በ1973 ዓ.ም. ተቀላቀሉ::

የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በእፅዋት ሳይንስ በቀድሞ ስሙ ከዓለማያ ኮሌጅ ባሁኑ ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በ1973 ዓ.ም ወስደዋል። እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1976 በእፅዋት ሳይንስ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዲሁም በ1978



በእጽዋት ማዳቀል እና ዘረመል ኢንጂነሪንግ አሜሪካ ከሚገኘው ፑርዱ ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል።

ፕሮፌሰር ገቢሳ በዚህ ዘርፍ የተሸለሙ ሁለተኛው አፍሪካዊ ናቸው። በአፍሪካ ናሽናሊቲ ሳይንስ ሂሮ ሽልማት ከተሸለሙ አፍሪካዊ ሰባት ተመራማሪዎችም አንዱ መሆን ችለዋል

በመቀጠልም ከፊል በረሃማ በሆኑ የትሮፒካል አካባቢዎች ከዓለም አቀፍ የአዝዕርት ምርምር ተቋማት ጋር ማሽላ ላይ በማተኮር ወደ አፍሪካ በመሄድ ምርምር ማድረጉን ተያያዙት:: ለአምስት ዓመታት ምርምሩን ካከናወነ በኋላ “ሃጂን ዶሮዋን” የተባለ የሱዳንን በረሃ የሚቋቋም እና ውጤቱም በ150% የላቀ ምርት የሚሰጠውን የተዳቀለ ማሽላን አገኙ:: ከዩ.ኤስ.ኤድ ጋር በመተባበርም ይህን ምርጥ ዘር በማምረት ለብዙ ገበሬዎች እንዲዳረስ የዘር ኢንደስትሪ እንቅስቃሴ አስጀመሩ::

ተመራማሪ ገቢሳ በተጓዳኝም Striga ወይም “ሟርተኛው አረም” ተብሎ የሚጠራውን የማሽላ ጠንቀኛ ጠላት ለማጥፋት ወደ ፐርዱ ዩኒቨርሲቲ በመመለስ ከተመራማሪ ጓደኛው ጋር በመሆን ጥናታቸውን ቀጠሉ:: Striga ወይም “ሟርተኛው አረም” 500,000 ዘሮችን የመበተን እና ዘሩም ከ10 - 20 ዓመት በአፈር ውስጥ የሚቆይ እና የዋናውን ተክል ዘር ሙሉ በሙሉ ወሮ ከጥቅም ውጭ የሚያደርግ አደገኛ አረም ነው:: በምርምራቸውም የዚህን አደገኛ አረም እና የማሽላን ኬሚካላዊ ትስስር በመለያየት ለመታደግ የቻሉ ታላቅ ሰው ናቸው::

ፕሮፌሰር ገቢሳ ኢጀታ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2011 የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ የዓለም አቀፍ የምግብ እና ግብርና ልማት ቦርድ አባል አድርገዋል ሾመዋቸዋል። ፕሮፌሰር ገቢሳ በተለያየ ጊዜ በማሽላ ላይ ባገኙት አስደናቂ ምርምር የተለያዩ ድቅል የሆኑ የማሽላ ዘሮችን መፍጠር የቻሉ ዕንቁ ኢትዮጵያዊ ናቸው::

ከ17 በላይ ታላላቅ ሽልማቶችን ያገኙ ሲሆን፤ የምግብና የእርሻ ድርጅት (ፋኦ) 2009 የወርልድ ፉድ ፕራይዝ ተሸላሚም መሆናቸው ይታወሳል። ፕሮፌሰር ገቢሳ በዚህ ዘርፍ የተሸለሙ ሁለተኛው አፍሪካዊ ናቸው። በአፍሪካ ናሽናሊቲ ሳይንስ ሂሮ ሽልማት ከተሸለሙ አፍሪካዊ ሰባት ተመራማሪዎችም አንዱ መሆን ችለዋል።

ፕሮፌሰር ገቢሳ ኢጀታ ከዚህ ቀደም ጥገኛ አረምን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን ለማዳቀል ለሚሰሩት ምርምር ከቢል እና ሜሊንዳ ጌትስ ግብረ-ሰናይ ድርጅት አምስት ሚሊዮን ዶላር አሸንፈዋል። በአሜሪካ የፑርዱ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ለሆኑት ገቢሳ እጄታ በቢልና መሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን የተሰጠው ድጋፍ ተመራማሪው አረም መቋቋም የሚችል የተዳቀለ ምርጥ ዘር እንዲያለሙ ለማስቻል ነው። በወቅቱ ፕሮፌሰር ገቢሳ ድጋፉ በተለይ ለታዳጊ ሀገሮች ግብርና ጠቃሚ እንደሆነ ተናግረው ነበር።

ፕሮፌሰር ገቢሳ ኢጀታ በዘርፉ በሰሩት ስራ ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት ለሚገኙ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ አፍሪካውያን የዕለት ጎርሳቸውን እንዲያገኙ አስችለዋል። በዚህ ታላቅ ውጤታቸው ከታላላቅ ተቋማት ጋር የሰሩ ሲሆን ለአብነት ለመጥቀስ ያህል ዩ.ኤስ. ኤድ፣ ሮክፌለር እና ጌትስ ፋውንዴሽን እንዲሁም አባል በመሆንም ከምግብና የእርሻ ድርጅት (ፋኦ)፣ የሳይንስ ካውንስል፣ የሳሳካዎ ግሎባል የቦርድ አባል እና የአሊያንስ ግሪን ሪቮሉሽን የክብር አባል በመሆን አገልግለዋል::

በርካታ ሽልማቶችን እና ሜዳሊያዎችን ያገኙ ሲሆን በ2009 የወርልድ ፉድ ፕራይዝ ተሸላሚ የዓለም ሎሬት ገቢሳ እንዲሁም ከቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ የብሔራዊ ጀግና የሚል ሽልማት አግኝተዋል:: 2011 ዓ.ም. የጅማ ዩኒቨርሲቲ የሳይንስ የክብር ዶክትሬት ተሸላሚም ናቸው:: በ2013 ዓ.ም. የቀድሞ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሃፊ ባን ኪሙን በሳይንስ ዘርፍ ሾመዋቸዋል:: ባሳለፍነው ዓመት 2015 ዓ.ም. የቀድሞ ትምህርት ቤታቸው የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ተሸላሚ አድርጓቸዋል።

ፕሮፌሰር ገቢሳ ኢጀታ ባሳለፍነው ሳምንት የአሜሪካን ብሔራዊ የሳይንስ ከፍተኛ የክብር ሜዳሊያ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን 21 አሜሪካውያን በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ዘርፎች ብሔራዊ የክብር ሜዳሊያ መሸለማቸውን አስታውቀዋል። ብሔራዊ የክብር ሜዳሊያ ከተሸለሙት መካከል ትውልደ ኢትዮጵያዊው ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ እንደሚገኙበትም ባይደን በማሕበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ ባወጡት ዝርዝር ላይ አመላክተዋል። በሳይንስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የሚሰጥ ሽልማት ነው።

በዚህም ፕሮፌሰር ገቢሳ ኢጀታ በሳይንስ ዘርፍ የአሜሪካ ብሔራዊ የክብር ሜዳሊያ ከፕሬዚዳንት ጆ ባይደን እጅ ተበርክቶላቸዋል። መምህርና ተመራማሪው ፕሮፌሰር ገቢሳ ኢጀታ ለሽልማቱ ያበቃቸው በከፍተኛ የምርምር ስራቸው የእፅዋት ዘረመል ምሕንድስና በመጠቀም በረሃማ የአየር ንብረት እና ነፍሳትን የሚቋቋሙ የአዝርዕት ዘሮችን በማግኘታቸው ነው።

ፕሮፌሰር ገቢሳ ከዘንድሮው ተሸላሚዎች መካከል አነስተኛ ገቢ ባላቸው አገራት ንጹህ የመጠጥ ውሃ በማቅረብ እንዲሁም በረሃን የሚቋቋሙ ዕጽዋት በማብቀል የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ እንደሆኑ ፕሬዚዳንት ባይደን የክብር ሽልማቱን ለፕሮፌሰሩ ባበረከቱበት ወቅት ተናግረዋል።

በሳይንስና ፖሊሲ ዘርፍ እንዲሁም በምጣኔ ሀብት ማሻሻል ረገድ ፕሮፌሰር ጋቢሳ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ለአርሶ አደሮች የተሻለ ሁኔታ መፍጠር የቻለ እንደሆነ እና አገራትን የሚያጠናክርም ነው በማለት ስለ ምርምራቸው በዋይት ሀውስ በተካሄደው የሽልማት ሥነ ሥርዓት ላይ ተገልጿል።

የዓለም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሰሩት ሥራ በዓለም መድረክ ከፍ ብለው የሀገራቸውን ስም ያስጠሩ ፀሐፊ፣ አርታኢ፣ መምህር፣ አማካሪ እና ተመራማሪ የዓለም ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኢጀታ ከሁለት መቶ በላይ የጥናት ጽሁፎችን ለሕትመት አብቅተዋል። አራት መፅሐፎችን የአርትኦት ስራ ሰርተዋል። ለ28 ዓመታት ያህል በአሜሪካ በሚገኘው ፐርዱ ዩኒቨርሲቲ ያገለገሉት የዓለም ሎሬት ፕሮፌሰሩ ዩኒቨርሲቲው አሉኝ ከሚላቸው ተመራማሪዎችም አንዱ ናቸው።

በምግብ ዋስትናው ዘርፍ በተመራማሪነት ባበረከቱት አስተዋጽኦ የዓለም የሎሬትነት ማዕረግን የተጎናጸፉት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኢጀታ፣” የዓለም ሕዝብ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የምግብ ፍላጎት እየጨመረ ይመጣል፤ ይህን ለመቋቋም ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና የምርምር ፈጠራ ውጤቶች በመጨመር ይህንን ችግር መቋቋም ግድ የሚል ነው” ይላሉ።

ፕሮፌሰር ገቢሳ ኢጀታ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ ኢንዲያና በሚገኘው ፐሪዱዩ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ ሲሆኑ፤ በዩኒቨርሲቲው የዓለም አቀፍ ምግብ ዋስትና ክፍል ዋና ዳይሬክተር ናቸው። እኛም ሀገራቸውን በሥራቸው ከፍ አድርገው ላስጠሩ የሀገር ካስማ ጉምቱ ምሁር ረዥም ዕድሜና ጤና እንመኛለን።

# ስፖርት





## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በሜዳው እንዲጫወት እየተሠራ ነው

ዓለማየሁ ግዛው

የኢትዮጵያ ወንዶች ብሔራዊ ቡድን የካፍና የፊፋን መስፈርት ያሟላ ስቴዲየም በማጣቱ ዓለም አቀፍ ጨዋታዎቹን በሌሎች ሀገራት ለማከናወን ከተገደደ ዓመታት ተቆጥረዋል። በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ለተለያዩ ወጪዎች የተዳረገ ሲሆን የብሔራዊ ቡድኑ ዋና አጋር ዋልያ ቢራም በዚሁ የተነሳ በአራት ዓመት የሚከፍለውን የ56 ሚሊዮን ብር ማቋረጡ ታውቋል። ፌዴሬሽኑ 15ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ከትናንት በስቲያ በአፍሪካ ኅብረት መሰብሰቢያ አዳራሽ ባደረገበት ወቅት ይህን ችግር በዝርዝር አቅርቧል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራ፣ የፊፋ እና ካፍ መስፈርት ያሟላ ስታዲየም በኢትዮጵያ ባለመኖሩ ለእግር ኳስ ልማት መዋል ያለበት ወጪ ለውጭ ሀገራት ጉዞና ተያያዥ ወጪ እየዋለ በመሆኑም መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት መፍትሔ እንዲያበጅ ጠይቀዋል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርም ችግሩን ተመልክቶ ብሔራዊ ቡድኑ በሀገሩ ሜዳ ጨዋታውን እንዲያደርግ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቁሟል። በጉባኤው ላይ የተገኙት የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት በዚህ ወቅት፣ እግር ኳስ በኢትዮጵያ ካለው ሕዝባዊ መሠረት ባሻገር በዓለም አቀፍ መድረክ ለገጽታ ግንባታና በስፖርት ዲፕሎማሲ ከሀገራት ጋር ያለንን ግንኙነት ለማሳደግ አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል። እግር ኳስ ፌዴሬሽኑ በእግር ኳስ ልማትና ከሌሎች ሀገራት እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች ትብብር ለመፍጠር የጀመረውን ሥራ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም አመልክተዋል።



በጉባዔው ላይ የተገኙት አምባሳደር መስፍን ቸርነት ብሔራዊ ቡድኑ በሜዳው እንዲጫወት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፣

ኢትዮጵያ በእግር ኳስ ካላት ታሪክ አንጻር ሀገሪቷን የሚመጥን ውጤት በዓለምና በአህጉር አቀፍ መድረክ ለማስመዝገብ ፌዴሬሽኑ በትኩረት መሥራት አለበት ነው ያሉት አምባሳደር መስፍን፣ መንግሥት የዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማኅበር (ፊፋ) እና የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) መስፈርትን ያሟላ ስታዲየም በማዘጋጀት የኢትዮጵያ ወንዶች ብሔራዊ ቡድን በሜዳው እንዲጫወት በልዩ ትኩረት እየሠራ ነው ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው ፌዴሬሽኑ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጋር በጋራ ለመሥራት የያዘውን በጎ ጅምር አጠናክሮ እንዲቀጥል መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ዓለም አቀፍ ውድድሮችን በሀገራችን ማስተናገድ ያልተቻለበት ብዙ ችግሮች ቢኖርም መንግሥት እነዚህን ችግሮች ፈቶ የስፖርት ቤተሰቡን ጥያቄ በአጭር ጊዜ ለመመለስ በትኩረት እየሠራ እንደሚገኝም ጠቁመዋል። የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አቅም፣ ልምድና እውቀት አናሳ እንደሆነና እግር ኳስን ለመሠረተችና ለመራች ሀገረ የማይመጥን እንደሆነም አንስተዋል። በዚህ ምክንያት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እየሰፉና ዓለም በደረሰበት ደረጃ መድረስ ሳይችሉ ቀርተዋል። እግር ኳስ ፌዴሬሽንን ጨምሮ ሁሉንም የስፖርት ማኅበራትን የመሩት በስፖርት ማዘውተሪያ ላይ ምን ሠራን የሚለውን መለስ ብለው ማየት እንደሚኖርባቸውም አስረድቷል። የሜዳና የሲቪል ሥራዎች አንድ ላይ ኮንትራት መስጠቱ ደረጃውን የጠበቀ የማውተሪያ ስፍራ እንዳይኖር በማድረጉ ችግሩን ለመፍታት እግር ኳስ ፌዴሬሽንን ጨምሮ የነበሩ ስህተቶችን ለማረም በጋራ እየሠሩ እንደሆነም ጠቁመዋል። የአዲስ አበባ ስታዲየም እድሳትምን ከፌዴሬሽኑ ጋር ክትትል በማድረግና የተፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት የቀደመ ስሙን ይዞ እንዲጠናቀቅ ጥሩ ሥራ እየተሠራ እንደሆነም አመላክተዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው አያይዘውም ከሁሉም ሀገር አቀፍ ማኅበራት አንጻር መንግሥት በማይመች ሁኔታ ውስጥ ሆኖም በሙሉ አቅሙ እግር ኳሱን እየደገፈ እንደሆነና በእግር ኳሱ የሚፈሰው ሀብት ጥንቃቄ ሊደረግበት እንደሚገባም አሳስበዋል። በእግር ኳሱ የሚወጣው ከፍተኛ ወጪ ጥንቃቄ ሊደረግበትና አሠራር ሊበጅለት ይገባል ሲሉም አሳስበዋል። በቂና ደረጃውን የጠበቀ የስፖርት ማዘውተሪያ ተገንብቶ ቀርቧል ማለት ባይቻልም የክልል ቢሮ ኃላፊዎች የፌዴሬሽኑንና የመንግሥትን ጭንቀትን በመረዳት በክልል የተጀመሩ የስፖርት ማዘውተሪያዎች ካለው ውስን ሀብት ተቀንሶ የሚጠናቀቁበትንና ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲሠሩ ጥረት መደረግ እንደሚኖረበትም ጠቁመዋል። በተጨማሪም በፌዴራል መንግሥት ደረጃ እየተሠሩና እየታደሱ ያሉ ስታዲየሞችም በፍጥነት ተጠናቀው ችግሩ እልባት ማግኘት እንዳለበት አክለዋል። ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የጀመረውን ለስፖርት ማዘውተሪያና ለኢትዮጵያ እግር ኳስ የሚያደርገውን ድጋፍና ክትትል በመቀጠል የስፖርት ቤተሰቡ የሚመኘውን ለውጥ ለማምጣት ከፌዴሬሽኑ ጋር በመሆን እንደሚሠራም ቃል ገብተዋል።


### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

<table>
<tr><td>1</td><td colspan="3">የአመልካች ስም፡- እውነቱ ሀይሉ ታመነ<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 11 የቤት ቁጥር. 1092,ቂርቆስ , አዲስ አበባ/ኢትዮጵያ</td></tr>
<tr><td>2</td><td colspan="3">የማመልከቻ ቁጥር፡- LTM/15055/2016<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 03/01/2016 E.C.</td></tr>
<tr><td rowspan="4">3</td><td rowspan="4">ምልክት፡-<br>UBUNTU<br>SCHOOL OF LIFE</td><td>4</td><td>የምልክቱ መግለጫ፡- የቃልና ምስል</td></tr>
<tr><td>5</td><td>የቀለም ዓይነት፡- ጥቁርና ነጭ</td></tr>
<tr><td>6</td><td>የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡- (SCHOOL OF LIFE)</td></tr>
<tr><td>7</td><td>ዓለም አቀፍ ምድብ፡-35</td></tr>
<tr><td rowspan="2">8</td><td colspan="3">ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች</td></tr>
<tr><td colspan="3">በኢኮኖሚ ቢዝነስ እና ኢንቨስትመንት በማህበራዊ በትምህርት ነክ ጉዳዮች የማማከር አገልግሎት (ምድብ 35)</td></tr>
</table>

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ሕግ ይጠየቃል።

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXIII No-051 21/2/2016 (1/11/2023)**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር dg-061 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0001099693 ወይንሸት ዘውዴ ዘመዴነህ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የተርን ኦቨር /ቲኦቲ/ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 299፣ 300 እና 500 የተሰራበት /ሦስት ቅጠል/ ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል።ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ።

**የግብር ከፋይ ስም ወይንሸት ዘውዴ ዘመዴነህ**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

ይግባኝ ባይ ወ/ሮ አልጋነሽ ሺፈራው እና መ/ሰጪዎች 1ኛ እነ ወ/ሮ መንበረ ለማ 2ኛ ወ/ሮ ብዙአየሁ ካሳሁን 3ኛ ወ/ሮ ዘሪቱ ካሳሁን አለሙ 4ኛ አቶ ሚኪያስ ፀጋዬ 5ኛ ወ/ሮ ገነት ካሳሁን አለሙ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ 5ኛ መልስ ሰጭ /ወ/ሮ ገነት ካሣሁን አለሙ ይግባኝ መጠየቁን አውቀው ለህዳር 03 ቀን 2016 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቀው ፌ/ከ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ተስፋ ኮከብ ት/ቤት አካባቢ 6ኛ ይግባኝ ፍትሐብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል። የማይቀርቡ ቢሆን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንገልጻለን።

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ሱራፌል ተስፋዬ ተፈራ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-91059 የተሽከርካሪው ዓይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNB7HD233915 ሞዴል ZZ3257N3447A የሞተር ቁጥር WD615.69*170217013247* የሊብሬ ቁጥር 0143135 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ13/2/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳውን ወድቆ ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ኢኳቶሪያል ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-50120 የተሽከርካሪው ዓይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNB8BA629487 ሞዴል ZZ3257N3447A የሞተር ቁጥር WD615.69-110507014897 የሊብሬ ቁጥር 16950 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ13/2/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳውን ወድቆ ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሚካኤል ደሳለኝ ጉግሳ የሠሌዳ ቁጥር አአ 02-01-C03257 የተሽከርካሪው ዓይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር MMBSTA13ANH010824 ሞዴል A13ASTHHL የሞተር ቁጥር 3A92 UKS0483 የሊብሬ ቁጥር 424389 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ13/2/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳውን ወድቆ ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የካ ቅ/ጽ/ቤት**